# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 337 ነሐሴ 7 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## “ሁላችንም ለሀገራችን ሌት ተቀን መሥራት ይኖርብናል”


- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የሕዝባችንን ሕይወት መቀየር የምንችለው በጠንካራ ሥራ ስለሆነ ስለዚህ ሁላችንም ለሀገራችን ሌት ተቀን መሥራት ይኖርብናል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የመገናኛ ሲኤምሲ መስመር የኮሪደር ልማት ተጠናቆ ለሕዝብ ክፍት መደረጉን አስመልክተው ባስተላለፉት መልዕክት እንዳሉት፤ በመሐል ላይ ቀላል የባቡር መስመር በመኖሩ እስካሁን ከተሠሩ የኮሪደር ልማት ሥራዎች ከበድ ያለ ነው።

“ሁላችንም ለሀገራችን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## አምስት ሚሊዮን “ኮደሮች”ለዲጂታል ግንባታ

ሄለን ወንድምነው

ዜና ትንታኔ

በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አምስት ሚሊዮን የኢትዮጵያ “ኮደሮች” መርሐ ግብርን ይፋ ማድረጋቸው የሚታወስ ነው።

አምስት ሚሊዮን የኢትዮጵያ ‘ኮደሮች’ መርሐ ግብር ከተባበሩት ዓረብ ኤሜሬትስ ጋር በመተባበር የሚተገበር ነው። የሥልጠና መርሐግብሩ ለሦስት ዓመታት የሚተገበር ሲሆን፤ አምስት ሚሊዮን ዜጎች ዘመኑን በዋጀው በዲጂታል ቴክኖሎጂ፣ በአርተፊሻል ኢንተለጀንስና በተያያዥ የዲጂታላይዜሽን ክህሎቶች ተጨባጭ ዕውቀት የሚያገኙበት መሆኑ ተገልጿል።

አምስት ሚሊዮን የኢትዮጵያ ‘ኮደሮች’ መርሐግብር ኢትዮጵያ ለምታደርገው የቴክኖሎጂ ሽግግር ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው?

በዲጂታል ቴክኖሎጂ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸው ወጣቶችን ከማፍራት አንጻር የሚያበረክተው አስተዋፅዖ ምን ይመስላል? በዲጂታል ቴክኖሎጂ አቅምና አጠቃቀም የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ ምን ያሳያል፤ ኢትዮጵያስ ምን መማር አለባት? በሚሉት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ላነሳቸው ጥያቄዎች የዘርፉ ምሁራን ምላሽ ሰጥተዋል።

አምስት ሚሊዮን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የግል የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎች ፋይዳ

ቃልኪዳን አሳዬ

ዜና ትንታኔ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሐምሌ 22 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ ባዋለው የውጭ ምንዛሪ መመሪያ ቁ.01/2016 መሠረት የግል የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎችን ለመክፈት የሚፈልጉ የሥራ ፈቃድ ማመልከቻ እንዲያቀርቡ ጥሪ አቀርቧል። ።

በዚህም በገበያ ላይ ተመሥርተው የውጭ ምንዛሪ በጥሬ ገንዘብ መሸጥና መግዛት የሚፈልጉ የግል የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎች ማቋቋም የሚፈልጉ በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም የሌላ ሀገር ዜግነት ያላቸው ትውልደ ኢትዮጵያውያን መስፈርት አሟልተው ወደ ሥራ መግባት እንደሚችሉ ተነግሯል። ።

አሠራሩ ተግባራዊ መደረጉ የውጭ ምንዛሪ ገበያን መሠረት ለማስፋትና ለማጠናከር እንዲሁም የውጭ

የግል የውጭ ምንዛሪ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# በቀጣይ ቀናት በሚኖረው ዝናብ የመሬት መንሸራተትና የወንዞች ሙላት ሊያጋጥም ይችላል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በሚቀጥሉት 20 ቀናት በሚኖረው ዝናብ የመሬት መንሸራተትና የወንዞች ሙላት እንዲሁም ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያጋጥም እንደሚችል የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ። ማኅበረሰቡ እና የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲሁም ጥንቃቄ ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስቧል።

የኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ለኢፕድ በላከው መግለጫ፤ በቀጣይ ቀናት በሚጥለው ዝናብ ቅጽበታዊ ጎርፍ፣ የመሬት መንሸራተትና የወንዞች ሙላት ሊያጋጥም ስለሚችል ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አሳስቧል።

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት በዓባይ ተከዜ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞ፣ ጊቤ፣ አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው የገናሌ ዳዋ እና ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች መካከለኛና በጣም ከፍተኛ እርጥበት እንደሚኖራቸው ተጠቅሷል።

ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የመሬት መንሸራተትና መሰንጠቅ፣ እንዲሁም የሰብል በጎርፍ የመጠረግ ሁኔታዎች እንዳይኖር መጠንቀቅ ያስፈልጋል ያለው ኢንስቲትዩቱ በመግለጫው፤ በተጨማሪም እርጥበት በሚበዛባቸው አካባቢዎች የሰብል በሽታ እንዳይከሰት ቅድመ ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባ ጠቁሟል።

እንደ ኢንስቲትዩቱ ገለጻ፤ በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ። አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በፀሐይ ኃይል ታግዞ ከሚፈጠረው ጠንካራ የሆነ የደመና ክምችት ምክንያት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በረዶና ነጎድጓድ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይከሰታል።

በሌላ በኩል ወደ ግድቦች የሚገባው ውሃ ከፍተኛ በመሆኑ አሁናዊ የውሃ ከፍታቸው አስጊ በሆነባቸው እንደ ፊንጫ፣ ጣና በለስ፣ ከሰምና ርብ የመሳሰሉት የኃይል ማመንጫ እና የመስኖ ግድቦች ላይ የቅርብ ክትትል ማድረግ እንደሚያስፈልግ በመግለጫው ተገልጿል።

በተመሳሳይ በሚቀጥሉት ስምንት ቀናት በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች አልፎ አልፎ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ የሚያስከትል ከባድ ዝናብ እንደሚኖር አስታውቋል።

በመደበኛ ሁኔታ በነሐሴ ሁለተኛው አስር ቀናት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ይበልጥ የሚጠናከሩበት መሆኑን የጠቀሰው ኢንስቲትዩቱ በመግለጫው፤ አልፎ አልፎ የሚኖረው ፀሐይ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ጠንካራ፣ ቁልል ደመና፣ በረዶ፣ ነጐድጓድ፣ መብረቅና ከባድ ዝናብ እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚያደርግ አመላክቷል።

በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የወቅቱ ዝናብ እንደሚቀጥል እና በአንዳንድ አካባቢዎች ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚኖርም ኢንስቲትዩቱ በመግለጫው ጠቁሟል።

የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው እርጥበት ለመኸር ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሣርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ኢንስቲትዩቱ ገልጿል።

# በአዲስ አበባ ከደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች አምስት ቢሊዮን ብር ተሰበሰበ

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ-፡ ከደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ከአምስት ቢሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን የአዲስ አበባ ከተማ ገቢዎች ቢሮ ገለፀ።

የከተማዋ ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ አቶ አደም ኑሪ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ ከ333 ሺህ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ከሐምሌ አንድ እስከ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ አምስት ቢሊዮን ብር ገቢ ተሰብስቧል።

ተቋሙ በዕቅዱ መሠረት እየሄደ ነው ያሉት አቶ አደም፤ 13 ሺህ ገደማ ግብር ከፋዮች ግብራቸውን ያልከፈሉ ናቸው ብለዋል።

የተቋሙ የሥራ ባሕሪ ለብልሹ አሠራር እና ሙስና ተጋላጭ እንደሚያደርገው የጠቀሱት ኃላፊው፤ ይህንን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ተናግረዋል።

ለአብነትም ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎች በመለየት ሙስና ለመከላከል አዳዲስ አሠራሮች በመዘርጋት እና የውስጥ ኦዲት በማድረግ ተጋላጭነትን ለመቀነስ እንሠራለን ብለዋል።

ኃላፊው እንዳሉት፤ ሊባክን የነበረ አስራ አራት ሚሊዮን ብር ሃብት ወደ መንግሥት ማስመለስ መቻሉን ጠቅሰው፤ ይህም ያለአግባብ ታክስ ማጭበርበርን ያካትታል ብለዋል።



አቶ አደም ኑሪ

የተጠቀሱት ብልሹ አሠራሮች ለመቆጣጠር አስራ አንድ ሺህ የተቋሙ ሠራተኞች የድግግሞሽ ሥልጠና መውሰዳቸውን ገልፀው፤ ይህም የነበረው ችግር ለማስቀረት የተደረገ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

ከአገልግሎት ጋር ተያይዞ 460 ሺህ ግብር ከፋዮች መስተናገዳቸውን ጠቅሰው፤ ከእነዚህ መካከል ሃምሳ አምስት ሺህ አዲስ ግብር ከፋዮች ናቸው ብለዋል።

በ119 ወረዳዎች ላይ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ሲስተናገዱ መቆየታቸውን ጠቅሰው፤ የደረጃ ሀ እና ለግብር ከፋዮችም በ16 ቅርንጫፎች መስተናገዳቸውን ገልፀዋል።

ተቋሙ የ2016 በጀት ዓመት አፈፃፀሙን መገምገሙን ጠቅሰው፤ የግብር አሰባሰብ በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በተደረገው ሂደት የግብር ውሳኔያቸው በስልካቸው እንዲደርሳቸው መደረጉ እና የደመወዝ ግብርም ወደ ቴክኖሎጂ አስገብተናል ብለዋል።

ተቋሙ ከ2016 በጀት ዓመት የታዩ ደካማ ጎኖችን በማሻሻል ጥንካሬውን በማስቀጠል ለ2017 በጀት ዓመት እንደሚሠራ ጠቁመው፤ በተለይ ሠራተኛው ማገልገል ቅድሚያ ተግባሩ መሆኑን ተረድቶ ኃላፊነቱ እንዲወጣ ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል። ።

ኅብረተሰቡም በሕጉ መሠረት መገልገል እንዲችል ባለድርሻ አካላትም ሚናቸው እንዲወጡ ሲሉ አስገንዝበዋል።

# ኢትዮጵያን ተመራጭ የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ ኤምባሲዎችን በመጠቀም መሥራት ያስፈልጋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡-ኢትዮጵያ ተመራጭ የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ አየር መንገድና ኤምባሲዎችን በመጠቀም መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን ኮሚሽነር ሌሊሴ ዱጋ ገለጹ።

የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽነር ሌሊሴ ዱጋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፡-የኢትዮጵያን የቱሪዝም መዳረሻዎችን አየር መንገድንና ኤምባሲዎችን በመጠቀም ማስተዋወቅ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ባላት ታሪክ፣ የተፈጥሮ ፀጋና ባሕል ልክ በቱሪዝም መዳረሻነት አትታወቅም ያሉት ኮሚሽነር ሌሊሴ፤ የኢትዮጵያን አየር መንገድና ኤምባሲዎችን በመጠቀም አዳዲስና ነባር የቱሪዝም መዳረሻዎችን ለዓለም ማስተዋወቅ ያስፈልጋል ብለዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢኒሼቲቭ የሆኑት የገበታ ለሀገር፣ ገበታ ለትውልድ ፕሮጀክቶች ለቱሪዝሙ ዘርፍ መነቃቃት መፍጠራቸውን ጠቅሰው፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ የወንጪ፣ የጨበራ ጩርጩራ የዝሆን ዳና፣ ጎርጎራና ሀላላ ኬላ መዳረሻዎች መልማታቸውን ገልጸዋል።

በመንግሥት ኢትዮጵያ ያላትን የተፈጥሮ ሀብት፣ ባሕል፣ ታሪክና ተነግሮ የማያልቅ ሀብት በመሠረተ ልማት ለመደገፍ እየተሠራ እንደሚገኝ በመግለጽ፣ የግሉ ባለሀብትም መንግሥት የጀመረውን ተከትሎ ወደ ቱሪዝሙ ዘርፍ በስፋት እየገቡ መሆኑን ተናግረዋል።

የመዳረሻዎችን መስፋፋት ተከትሎ የሀገር ውስጥ ቱሪዝም እንቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ እየተነቃቃ ነው ያሉት ኮሚሽነሯ፣ ነገር ግን ኢትዮጵያ የረዥም ዘመን የታሪክ ባለቤት ብትሆንም በቱሪዝም መዳረሻነት ለመታወቅ ጠንካራ የማስተዋወቅ ሥራዎችን ሊሠራ እንደሚገባ ገልጸዋል።

በቱሪዝሙ ዘርፍ ኢትዮጵያን የሚመጥን የገበያና የማስታወቂያ ሥራዎች በትኩረት ሊሠሩ እንደሚያስፈልግ በመግለጽ፣ በተለይም ቻይናን፣ በዓረቡ ዓለምና የአፍሪካ ሀገራት ላይ በትኩረት መሠራት እንዳለበት አመላክተዋል።

የኢትዮጵያን አየር መንገድና ኤምባሲዎችን በመጠቀም የቱሪዝም መዳረሻዎችን ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ማስተዋወቅ እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፣ ኢትዮጵያን እንደ መሸጋገሪያ የሚጠቀሙ ተጓዦች ላይ በመሥራት የቱሪዝም መዳረሻዎችን እንዲጎበኙ ማድረግ ያስፈልጋልም ብለዋል።



ኮሚሽነር ሌሊሴ ዱጋ

የአዲስ አበባ የኮሪደር ልማት የከተማ ቱሪዝምን አቅጣጫ የሚቀይርና ለከተማ ቱሪዝም መነቃቃት አስፈላጊ መሆኑን የገለጹት ኮሚሽነሯ፣ በልማቱ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ መደገም መቻል አለበት ብለዋል።

የኮሪደር ልማቱ በዓለም አቀፍ የከተማ ቱሪዝም ተወዳዳሪነትን እንደሚያጎናጽፍ በመግለጽ፣ ከተማን ንጹሕ ምቹ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ የመንገድ ዳር ምግቦች፣ የሕዝብ መዝናኛና መፀዳጃ ስፍራዎች ለከተማ ቱሪዝም ወሳኝ መሆናቸውን አስረድተዋል።

በፅዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ መሠረት ከተሞችን ፅዱ ለማድረግ የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ጠቅሰው፣ በአዲሱ ዓመት እንደ ኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን ከተሞችን ተወዳዳሪ ለማድረግ ተመሳሳይ የኮሪደር ልማቶች እንደሚሠሩ ጠቁመዋል።

# “የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ላይ ስር ነቀል ለውጥ እንደሚያመጣ ይጠበቃል”

- ኢንጂነር ግርማ ሀብተማሪያም
የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጮች ማኅበር ፕሬዚዳንት

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ላይ ስር ነቀል ለወጥ እንደሚያመጣ የሚጠበቅ መሆኑን የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጮች ማኅበር ፕሬዚዳንት ኢንጂነር ግርማ ሀብተማሪያም ገለጹ። የሀገር ውስጥ ተቋራጮች ተወዳዳሪ እንዲሆኑ አቅም በሚያሳድግ መልኩም በጥናት የተደገፈ ድጋፍ እንደሚያሻውም አመላክተዋል።



የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ኢንጂነር ግርማ ሀብተማሪያም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በዘርፉ ቀደም ሲል ያጋጥሙ የነበረው የውጭ ምንዛሪ እጥረት ችግር የሚቀርፍ ነው። ይህም የኮንስትራክሽን ዘርፉ በውጭም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የግንባታ እቃዎችን በቀላሉ እንዲያገኝ ያስችለዋል።

ማሻሻያው የኮንስትራክሽን ግብዓት አስመጪ ድርጅቶች ከባንኮች በቀላሉ የውጭ ምንዛሪ የሚያገኙበትን ዕድል የሚፈጥር መሆኑን ገልጸው። ይህም በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት እስካሁን ይታይ የነበረውን የኮንስትራክሽን ግብዓት ችግርን ይፈታል ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

“የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ባለድርሻ እንደመሆናችን ማሻሻያው በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤታማ እንዲሆን ከፍ ያለ ፍላጎት አለን ያሉት የማኅበሩ ፕሬዚዳንት፣ ማሻሻያው በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት የቆሙ ፕሮጀክቶች በአጭር ጊዜ እንዲጠናቀቁ ለማድረግም ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖረዋል ብለዋል።

የግንባታውን ዘርፍ ከባሕላዊ እና ከልማዳዊ አሠራር ወደ ቴክኖሎጂ ማሳደግ እንደሚያስፈልግም ጠቅሰው፣ በዚህ በኩል የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ከፍተኛ ለውጥ ያመጣል ተብሎ እንደሚጠበቅ የማኅበሩ ፕሬዚዳንት አስታውቀዋል።

የሀገር ውስጥ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ተወዳዳሪ ሆኖ ከሀገር አልፎ ወደ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራትም የመሄድ ፍላጎት እንዳለው ጠቅሰው፣ ማሻሻያው በዚህ ረገድም ጉልህ ድርሻ እንደሚኖረው ገልጸዋል።

ማሻሻያው ተከትሎ በገበያው ላይ ቀደም ብለው የገቡ የኮንስትራክሽን ግብዓቶችና መሣሪያዎች ላይ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ እንዳይደረግ ከፍተኛ ቁጥጥር እና ክትትል መደረግ እንዳለበት አመላክተዋል።

ማሻሻያው በአተገባበር ብዙ ፈተናዎች ሊያጋጥሙት ይችላሉ ሲሉም ስጋታቸውን ጠቁመው፣ በዚህ ዓይነት አሠራር ለጉዳት የተዳረጉ ሀገሮች ዓይነት ችግር እንዳያጋጥመን በትግበራው ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል ሲሉም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ሥራ ተቋራጮች ሥራ በጥራት አይጨርሱም፤ የውጭዎቹ በጥራት ይጨርሳሉ” ሲባል እንደሚሰማም ጠቅሰው፣ በቂ ድጋፍ ከተደረገላቸው የኢትዮጵያ ተቋራጮችም የውጭዎቹ የሚሠሩትን ለመሥራት የሚያስችል አቅም እንዳላቸው ገልጸዋል። በቅርቡም አንዳንድ ሥራ ተቋራጮች የውጭ ሥራ ተቋራጮች ከሚሠራቸው ጥራት በላይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሠርተው ያስረከቡበት ሁኔታ መኖሩንም ጠቅሰዋል።

ፕሬዚዳንቱ እንዳብራሩት የሀገር ውስጥ ሥራ ተቋራጭ ተወዳዳሪ ሆኖ ወደ ውጭ ለመውጣት በመጀመሪያ ደረጃ ሀገር ውስጥ ያለውን ገበያ ማሸነፍ እና ራሱን ማብቃት ያስፈልጋል።

# ተማሪዎች በዕረፍት ጊዜያቸው

**ነፃነት ዓለሙ**

**ዜና ሐተታ**

የክረምት ወቅት ለተማሪዎች ረጅሙ የእረፍት ጊዜ ነው። ይህን የእረፍት ጊዜ ተማሪዎች በምን መልኩ ያሳልፉታል የሚለው የአብዛኛው ወላጅ ጥያቄ ነው። በተለይም ከአኗኗራችን መቀያየርና ከቴክኖሎጂ መስፋፋት ጋር ተያይዞ ልጆች ከእኩዮቻቸው ጋር ይልቅ ስክሪን በመመልከት የሚያሳልፉት ጊዜ እየሰፋ መጥቷል።

የሥነልቦና ባለሙያ አቶ አቤል እስጢፋኖስ እንደሚሉት አሁን አሁን ልጆች ላይ ለሚታዩ የተግባቦት እድገት ውስንነቶች ስክሪን ላይ ረጅም ሰዓት ማሳለፍ አንዱ ምክንያት ነው። እንደእርሳቸው ገለፃ በእኛ ሀገር ደረጃ ልጆች ትምህርት የሚጀምሩበት ወይንም ወደ ቅድመ መደበኛ ትምህርት የሚገቡበት ዕድሜ አራት ዓመት ነው።

በዚህ ዕድሜ ክልል ላይ ያሉ ልጆች የጀመሩበትን ዓመት ትምህርት አጠናቀው ክረምትን ቤት ውስጥ በምን ያሳልፉ በምንልበት ጊዜ በተለይም ኮንዶሚኒየም ወይንም አፓርታማ ላይ የሚኖሩ ወላጆች እንደድሮ ልጆቹ ራሳቸው ወጥተው እንዲጫወቱ ላይፈቅዱ ይችላሉ ልጆች ቴሌቪዥን እያዩና ጌሞችን እየተጫወቱ ረጅም ሰዓት ያሳልፋሉ።

ይህ ደግሞ ተግባቦታቸውና ማኅበራዊ ግንኙነታቸው ሊያድግ የሚችልበት ዕድሜ ላይ ከመሆናቸው አንፃር አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል ባይ ናቸው። በዚህ የዕድሜ ክልል ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ዕድሜ ላይ ላሉ ልጆች ስክሪን ላይ ረጅም ሰዓት ማሳለፍ አሉታዊ ተፅዕኖው የጎላ ከመሆኑ አኳያ ወላጆች የልጆቻቸው ስክሪን አጠቃቀም ላይ ገደብ ማበጀት እንደሚገባቸው ይገልፃሉ።

ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ባይችሉ እንኳ ከአንድ ሰዓት የበለጠ ጊዜ ስክሪን ላይ እንዳያሳልፉ የሚመከር መሆኑን ጠቅሰው፤ ለምሳሌ አንድ ልጅ በተፈቀደለት አንድ ሰዓት የሆነ አጭር ፊልም ቢያይ እዛ ፊልም ላይ ምን እንዳየ መጠየቅና ታሪኩን ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው እንዲናገር ማድረግ ይገባል።

አልያም ልጁ ስክሪኑን ብቻ እንዲያይ ከማድረግ ይልቅ ሙዚቃዎችን ከፍተን ከሙዚቃው ጋር እየተንቀሳቀሰ ሌሎች ችሎታዎችን እንዲያዳብር በማድረግ ወደ ጠቀሜታ የምናመጣበት መንገድ ቢኖር የተሻለ እንደሚሆንም ባለሙያው ይመክራሉ።

ይህ እንዳለ ሆኖ የተማሪዎች የክረምት ውሎ በምን መልኩ ማለፍ አለበት ለሚለው ጥያቄ ወላጆች ልጆቻቸው የሚወዷቸውን ነገሮች እያዩ ለምሳሌ የእግር ኳስ፣ የሙዚቃ፣ የስዕል እና ሌሎችም ፍላጎቶች ካላቸው የክረምት ጊዜያቸው እነዚህን ፍላጎቶቻቸውን የሚያዳብሩበትን መንገድ ታሳቢ ያደረገ ሊሆን እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የተለያዩ የክረምት ፕሮግራም ሥልጠናዎች እንዲወስዱ ማመቻቸትም ራሳቸውን በተሻለ እንዲገልፁ፣ አዳዲስ ነገሮችን እንዲቀስሙና ፍላጎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ተመራጭ መሆኑንም ይናገራሉ፡

ክፍያ አንፃር ሁሉም ወላጅ ይህን ማድረግ ላይችል ስለሚችል መናፈሻዎችና የሕዝብ መዝናኛ ቦታዎች ሄደው እንዲያሳልፉ ማድረግም የተሻለ ነው ይላሉ። ይህም ከሌሎች ጋር በመግባባት የቋንቋ፣ የተግባቦት እና የማኅበራዊ ግንኙነታቸውን እንዲያጎለበቱ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይገባል ነው ያሉት።

በተጨማሪም ወላጆች የልጆቻቸውን የትምህርት ውጤት በማየት ደከም ያሉባቸውን ትምህርቶች እንዲያጠኑ ማድረግ እንደ አንድ የክረምት ጊዜ ማሳለፊያ ከመሆኑ ባሻገር ለቀጣይ ዓመት ትምህርትም ከእኩዮቻቸው ጋር ባልተናነሰ ዝግጁ እንደሚያደርጋቸው ገልፀው፤ ሙሉ የክረምት ጊዜያቸውን ግን ከትምህርት ጋር የተያያዙ ነገሮች ላይ ብቻ እንዲያሳልፉ ማድረግ ብቻውን ጠቀሜታ ስለማይኖረው ከዛ ጎን ለጎን በተቻለ አቅም አዳዲስ ነገሮችን የሚሞክሩበትን ጊዜ ማመቻቸት እንደሚያስፈልግ ያብራራሉ።

በአጠቃላይ የክረምት ወይንም የእረፍት ጊዜያቸው ተማሪዎች ያላቸውን የቋንቋ እድገት፣ የጨዋታ ክህሎት እና የማኅበራዊ ግንኙነታቸውን ቢያዳብሩበት ይመረጣል። ምክንያቱም ውጤቱ የአዕምሮ ብቃታቸው የተሻለ እንዲሆንና ነገሮችን ከብዙ አቅጣጫዎች ማየት እንዲችሉ የሚያደርግ መሆኑን ያስረዳሉ።

ከዚህ አኳያ ወላጆች ልጆቻቸው አዳዲስ ክህሎቶችን እንዲለምዱ የሚያደርጉበት ጊዜ ቢሆን የተሻለ ነው ሲሉ የሥነልቦና ባለሙያው አቶ አቤል እስጢፋኖስ አብራርተዋል።

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት ወይዘሮ ዮርዳኖስ ተክሌ ተማሪዎች በእረፍት ጊዜያቸው ለተሻለ የትምህርት ውጤት ብቻ ሳይሆን ለተሻለ ሁለንተናዊ ዕድገታቸውም ማንበባቸው ወሳኝ ሚና አለው ።

ተማሪዎች የክረምት ወይም የእረፍት ጊዜያቸውን ትምህርት ነክ የሆኑ መጽሐፍቶችን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም አይነት መጽሐፍት ከመዝናናቱና እረፍት ከማድረጉ ጎን ለጎን ቢያነቡ ለቀጣይ ዓመት ትምህርት በአዲስ መንፈስ ከመዘጋጀት አንፃር ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል በማለት ሀሳባቸውን ሰጥተውናል።

# ኢንስቲትዩቱ ባሕላዊ መድኃኒቶች በዘመናዊ መንገድ ተመርተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ እየሠራ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በባሕላዊ መንገድ ለመድኃኒትነት የሚውሉ ሃገር በቀል ዕፅዋት ላይ ምርምር በማድረግ በዘመናዊ መንገድ ተመርተው ወደ ገበያ እንዲቀላቀሉ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን የአርማወር ሃንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት ገለጸ።

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ፕሮፌሰር አፈወርቅ ካሡ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ኢንስቲትዩቱ በባሕላዊ መንገድ ለመድኃኒትነት የሚውሉ ሃገር በቀል ዕፅዋት ላይ ምርምር በማድረግ በዘመናዊ መንገድ ተመርተው ወደ ገበያ እንዲቀላቀሉ ለማድረግ እየሠራ ነው። እነዚህ መድኃኒትነት ያላቸው ዕፅዋት በተቋሙ ግቢ ውስጥ በተዘጋጀላቸው መካነ-ዕፅዋት እየተተከሉ ይገኛሉ።



ፕሮፌሰር አፈወርቅ ካሡ

ይህም ዕፅዋቱ እንዳይጠፉ ጥበቃ ለማድረግ እና ተመራማሪዎችም በቀላሉ እንዲያገኟቸው እንደሚያስችል ያስረዱት ፕሮፌሰር አፈወርቅ፤ ኢንስቲትዩቱ በ2017 በጀት ዓመት የባሕል ሕክምና ምርምር ላይ በትኩረት እንደሚሠራ ገልጸዋል። ለዚህም ከዩኒቨርሲቲዎች እና ከጤና ቢሮዎች ጋር በጥምረት እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

በዚህም የክልልና የከተማ ጤና ቢሮዎች በየአካባቢያቸው ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በትብብር መሥራት እንዲችሉ ክላስተር መደራጀቱን የገለጹት ፕሮፌሰር አፈወርቅ፤ ለአብነት የምሥራቅ ኢትዮጵያ የጤና ክላስተር በሚል የሰመራ ዩኒቨርሲቲን እና ከአፋር ጤና ቢሮ ጋር በክላስተር የማደራጀት ሥራ መሠራቱን ገልጸዋል።

ከሐረማያ ዩኒቨርሲቲ፣ ከኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ፣ ከድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ፣ ከቀብሪ ደሐር ዩኒቨርሲቲ፣ ከጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም ከኦሮሚያ፣ ከድሬዳዋ፣ ከሐረር፣ ከሶማሌ ጤና ቢሮዎች ጋር በመሆን በየአካባቢው ያሉ የባሕል ሕክምና እውቀቶችን ከዘመናዊ ሕክምና ጋር ለማዋሓድ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ይህም በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል የሚከናወን ተግባር ነው። ሀገራዊ የሕክምና መድኃኒቶችን የማምረት አቅም ለማሳደግ ሀገር በቀል እውቀቶች ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል ያሉት ፕሮፌሰር አፈወርቅ፤ የባሕል ሕክምና ምርምር የሁሉም ዩኒቨርሲቲዎችና ጤና ቢሮዎች አጀንዳ መሆኑ ለዘርፉ ትልቅ ትኩረት የተሰጠው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል ብለዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ ኢንስቲትዩቱ ከባሕል ሕክምና አዋቂዎች ማኅበር ጋር በጥምረት ይሠራል። ። በ2017 በጀት ዓመት ሳምንታት የሚቆይ መድረክ እንደሚኖር ጠቁመዋል። ይህም የእርስ በእርስ እውቀቶች እና የልምድ ልውውጥ መድረክ ይሆናል ነው ያሉት።

በዚህም በጋራ መሥራት የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች ከመለየት ባለፈ ተግባራዊ የሚደረጉበት ሁኔታዎች ላይ ውይይት ይደረጋል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በዚህም ኢንስቲትዩቱ የባሕል ሕክምና ምርምርና ልማት የሚመለከት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ይሠራል። ይህም ለቀጣይ ሥራዎች በር እንደሚከፍት ተናግረዋል።

# “ሁላችንም ለሀገራችን ሴት ተቀን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በዚህ ሥራ የእግረኛ መንገድ፣ የአረንጓዴ ልማት፣ የሕንጻ ውበት፣ የብስክሌት መንገድ፣ አነስተኛ ፓርኮችና እንዲሁም የስፖርት ማዘውተሪያዎችን ያካተተ ነው። ይህም የሰፋ ነገር እንድናይ በማድረግ የሰፋ እሳቤ እንድንይዝ ያደርጋል ብለዋል። ከዚህ በፊት ለሕዝብ ማዘውተሪያ ተብለው የሚተዉ ቦታዎች በሕገወጥ መንገድ የሚቸበቸብና ጥቂቶች የሚበለፅጉበት እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን በተሠሩ ሥራዎች ግን ሕዝቡ የሚዝናናበትና የሚያሰላስልበት ቦታ ማድረግ ተችሏል።

በቀጣይነትም አካባቢውን የትራፊክ ፍሰት የሚመጥን ማሳለጫ ለመሥራት እንደሚያስፈልግም ጠቁመው፤ ለዚህም አስፈላጊው ውይይትና ምክክር እየተደረገ ነው ብለዋል።

እስካሁን የተሠራው ሥራ አስደሳች መሆኑን ጠቁመው፤ በዚህ መርካት ሳይሆን ወደፊት በርካታ የቤት ሥራ እንዳለብን ማሰብ ይኖርብናል። የኮሪደር ሥራውም በአዲስ አበባም በክልል ከተሞችም ተጠናክሮ ይቀጥላል።

የከተማዋ ነዋሪዎችም ለሥራው የሚያደርጉትን ድጋፍ፣ ትብብርና ትዕግስት አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጠይቀው፤ ሕዝባችን ሕይወት መቀየር የምንችለው በጠንካራ ሥራ ስለሆነ ከለዚህ ሁላችንም ለሀገራችን ሴት ከቀን መሥራት ይኖርብናል ብለዋል።

ከዓመታት በፊት የዚህ ሥራ ጥናት ሲደረግ የከተማዋ የደን ሽፋን ከሦስት በመቶ በታች እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ላይ በተሠሩ ሥራዎች ሽፋኑ ወደ 20 በመቶ እየተጠጋ ነው። ይህን ሥራ አጠናክረን ከቀጠልን በጥቂት ዓመታት ውስጥ መዲናዋን ውብና ለኑሮ የምትመረጥ ማድረግ እንችላለን። በሁሉም መስክ የተጀመረውን ሥራ አጠናክረን በመቀጠልም ለልጆቻችንም የበለፀገች ኢትዮጵያን ማስረከብ እንችላለን ብለዋል።

# አምስት ሚሊዮን “ኮደሮች”ለዲጂታል...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚኒስትሩ ከፍተኛ አማካሪ አብዮት ባዩ (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ በአሁኑ ወቅት የዲጂታል ክህሎትና እውቀት ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ወሳኝ ነው። በጤና፣ በትምህርት፣ በግብርና እና በማንኛውም መስክ የሚሠሩ ሥራዎች የዲጂታል ክህሎትን ይፈልጋሉ። የመግባቢያ፣ የመገልገያ እና የማምረቻ መሣሪያዎችም በዲጂታል ቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

በዚህም ማንኛውም ሰው ሥራውን ለማከናወን የዲጂታል ክህሎት ያስፈልገዋል። የዲጂታል እውቀትና ክህሎት በሌለበት ሁኔታ የሀገርን ኢኮኖሚ ሊደግፍ የሚችል የሰው ኃይል ማፍራት ከባድ ነው ሲሉ ይናገራሉ።

ኢትዮጵያ በዲጂታል ክህሎት ወደኋላ ቀርታለች የሚሉት አብዮት (ዶ/ር)፤ አሁን ላይ አምስት ሚሊዮን ወጣቶችን በዲጂታል ለማሠልጠን እየተደረገ ያለው ጥረት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ግንባታ ወሳኝ ነው። በርከት ያሉ ወጣቶችን በዲጂታል ቴክኖሎጂ ማሠልጠን ካልተቻለ የሀገሪቱ የዲጂታል ክህሎት ክፍተት እያደገ ስለሚሄድ የአምስት ሚሊዮን ኮደሮች ሥልጠናን ሁሉም ትኩረት በመስጠት ሊጠቀምበት ይገባል ይላሉ።

የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ ብቻ ሳይሆን ከጎረቤት ሀገራቶችም አንጻር ወደኋላ ቀርታለች ብሎ ያስቀምጣል። ኢትዮጵያን በዲጂታል ክህሎት ከሌሎች ሀገራት ጋር ተወዳዳሪ ለማድረግ በርከት ያሉ ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ክህሎት ሥልጠና ቀርጾ መተግበር እንደሚገባ ስትራቴጂውን ዋቢ አድርገው ይገልጻሉ።

ለዚህ ደግሞ የአምስት ሚሊዮን ዲጂታል ክህሎት ፕሮግራም የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን እውን ለማድረግ መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑን በመግለጽ፤ በቀጣይም የዲጂታል ክህሎት ያላቸው ዜጎችን ለማፍራትና መሠረተ ልማትን ለማስፋፋት ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ በአፅንዖት ያስረዳሉ።

የዲጂታል ክህሎት በዋናነት መሠረታዊ የኮምፒውተር እውቀት፣ ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅሞ ሥራ መሥራት መቻልንና መተግበሪያዎችን ማልማትን ያጠቃልላል የሚሉት አብዮት (ዶ/ር)፤ መሠረታዊ የኮምፒውተርን ክህሎትን ሁሉም ሰው ሊያውቀው ይገባል። በዚህም አብዛኛው ሀገራት ዜጎቻቸው መሠረታዊ የኮምፒውተር ክህሎት እንዲኖራቸው እያደረጉ መሆኑን ያመላክታሉ።

ወደሥራ የሚሠማራው የሰው ኃይል ውጤታማ ሥራን ማከናወን የሚችለው ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን ሲጠቀም በመሆኑ፤ የዓለም ሀገራት የትምህርት ሥርዓት የዲጂታል ክህሎትን ያካተቱ ናቸው። በዚህም ማንኛውም ሰው በሚያልፍበት የትምህርት ተቋማት በቂ የዲጂታል ክህሎት አግኝቶ እንዲወጣ እያደረጉ ስለመሆኑ ይናገራሉ።

ሀገራት ራሳቸውን ለመጠበቅ፣ ጥቃት ለመከላከል እና ኢኮኖሚያዊ እድገታቸውን ለማፋጠን አዳዲስ መተግበሪያዎችን የሚያለሙ እና በቂ የዲጂታል ክህሎት ያላቸው ዜጎችን ማፍራት ላይ ትኩረት ማድረጋቸውን ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያ ለዘመናት ስትከተለው የቆየችው የዲጂታል ፖሊሲ፣ መሠረተ ልማት አለመስፋፋቱ እና ኢትዮ ቴሌኮም በገበያ የሚመራ ባለመሆኑ ወደኋላ እንድትቀር ምክንያት መሆኑን በመግለጽ፤ አሁን ላይ ኢትዮጵያን ተወዳዳሪ ለማድረግ የቴሌኮም ሴክተሩን ለገበያ ክፍት የማድረግ፣ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎችን ወደገበያ የማስገባት፣ ሥርዓተ ትምህርቱን (ካሪኩለሙ) የመቀየር፣ በመንግሥት አሠራር ዲጂታል አሠራርን አስገዳጅ ማድረግ፣ የዲጂታል ክፍያዎችን በዲጂታል የማድረግ እና ሌሎች በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። በቀጣይም እነዚህን እና ሌሎች ሥራዎችን ትኩረት በመስጠት መተግበር ከተቻለ ኢትዮጵያ በቴክኖሎጂ ካደጉ ሀገራት ተርታ መሰለፍ ትችላለች ሲሉ ያብራራሉ። ።

የአምስት ሚሊዮን ኮደሮች ሥልጠና መርሐግብር ተጠቃሚዎች መሠረታዊ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ክህሎትን ለማግኘት፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ እና ሌሎች በርካታ ጥቅሞችን የሚያስገኛቸው በመሆኑ ትኩረት ሰጥተው ሊጠቀሙበት እንደሚገባ ያሳስባሉ።

ፕሮግራሙን ለማስፈጸም በፌዴራል እና በክልል የሚመራ ኮሚቴ መቋቋሙን ገልጸው፤ ወጣቶች ሥልጠናውን በአግባቡ እንዲወስዱ ድጋፍና ክትትል የማድረግ ሥራ ይሠራሉ ይላሉ።

በአምስት ሚሊዮን ኮደሮች መርሐ ግብር ኦላይን የሚሰጡ ትምህርቶችን መከታተል የሚችል ማንኛውም ወጣት መሳተፍ የሚችል ሲሆን እስካሁን ከ92 ሺህ በላይ ወጣቶች ተመዝግበው ሥልጠናውን እየከታተሉ መሆኑን ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ወርቁ ጋቸና (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ በሀገሪቱ የሚገኙትን በርካታ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድሎች በአግባቡ በመጠቀም ካደጉ ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ በትብብር መሥራት ይገባል ይላሉ።

ኢትዮጵያ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ካደጉ ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ እያደረገች ያለው ጥረት የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ማቋቋሟ፣ አምስት ሚሊዮን ‘ኮደሮች’ ይፋ መሆኑ፣ በፖሊሲ የታገዘ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ስትራቴጂ መፅደቁ እና ሌሎች በርካታ ሥራዎች መሥራታቸው የሚበረታታ መሆኑን ያስረዳሉ።

የግልና የመንግሥት ተቋማት የዲጂታል ዳታ ክምችትን በአግባቡ በማስቀመጥ፣ ልምድና ተሞክሮ በመለዋወጥ፣ አገልግሎት አሰጣጣቸውንና መረጃ አያያዛቸውን በቴክኖሎጂ በመደገፍ ሀገሪቱ የምታወጣውን የጊዜና የሀብት ብክነት እንደሚገባም ያስረዳሉ።

ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥና መረጃ አያያዝን ዲጂታላይዝድ ማድረግን እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ በእቅዳቸው ውስጥ በማካተት ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት ይጠበቅባቸዋል የሚሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ሁሉም ተቋማት ከኋላ ቀር አሠራር በመውጣት በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የሚመለከተው ባለድርሻ አካል በፖሊሲ ሊደግፋቸው ይገባል ሲሉ በአፅንዖት ይናገራሉ።

የዓለም ሀገራት የቴክኖሎጂ ዘርፍን የመወዳደሪያ መስፈርት አድርገው በትኩረት እየሠሩበት ነው የሚሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ግብርና፣ ጤና፣ ፋይናንስ እና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎችን ከቴክኖሎጂ ጋር በማዛመድ አገልግሎት አሰጣጣቸውንና መረጃ አያያዛቸውን በማዘመንና በማቀላጠፍ ምርትና አገልግሎታቸውን ማሳደግ ችለዋል ሲሉ አብራርተዋል።

የቴክኖሎጂ አጠቃቀም አቅምን በማሳደግ፣ አሠራርን ለማዘመን፣ ሀብትና ጊዜን ከብክነት ለመታደግና ለሥራ ዕድል ፈጠራ የኮደሮች ሥልጠናው ከፍተኛ ፋይዳ አለው ሲሉ ይገልጻሉ።

አምስት ሚሊዮን ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርገው የኮደር ሥልጠና በሀገሪቱ ያሉትን ዳታዎች ዲጂታላይዝድ ለማድረግ ከፍተኛ ፋይዳ አለው የሚሉት በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የብሔራዊ ኔትዎርክ ማሳለጫ ፕሮጀክት መሪ አቶ ዳንኤል አድኖ ናቸው።

እንደ አቶ ዳንኤል ገለጻ፣ ሀገሪቱ ለቴክኖሎጂ የምታወጣውን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር የውጭ ምንዛሪ በሀገር ውስጥ ለማስቀረትና የሥራ ዕድልን ለመፍጠር ይረዳል። በሥልጠናው የሚለሙ መተግበሪያዎችን የሚጠቀሙ ብቻ ሳይሆን መተግበሪያዎችን የሚያለሙ፣ በዲጂታል ክህሎትና እውቀት ያላቸው ዜጎችን ለማፍራት ያስችላል ይላሉ።

በአሁኑ ወቅት በርካታ የዓለም ሀገራት በወረቀት ከሚሠሩ ሥራዎች በመውጣት ዲጂታላይዜሽን እና ሰው ሠራሽ አስተውሎትን እየተገበሩ ይገኛሉ። ኢትዮጵያም አምስት ሚሊዮን ዜጎቿን ኮዲንግ ካሠለጠነች ዓለም በቴክኖሎጂ የደረሰበት ደረጃ መድረስ ትችላለች ሲሉ ያስረዳሉ።

የአምስት ሚሊዮን የኮደር ሥልጠናው ኢትዮጵያ ለምታደርገው የቴክኖሎጂ ሽግግር ድልድይ መሆኑን በመግለጽ፤ የቴክኖሎጂ ሽግግሩ በሀገር ውስጥ ባለሙያዎች ሲሠራ የበለጠ ውጤታማ ያደርጋል። የኢንዱስትሪ፣ የሚዲያ፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርና እና ሌሎች ተቋማት ከቴክኖሎጂ ጋር ጥብቅ ትስስር ያላቸው በመሆኑ ሀገሪቱ በርካታ የቴክኖሎጂ ባለሙያዎችን ማፍራት ለነገ የማይባል ተግባር መሆኑን ያስረዳሉ።

እንደ አቶ ዳንኤል ገለጻ፣ የሕንድ፣ የቻይና እና የሌሎች ሀገራት ኢኮኖሚ ከቴክኖሎጂ ጋር የተሳሰረ ነው። አንዳንድ ሀገራት በቴክኖሎጂ ከማደጋቸው የተነሳ ከሌሎች ሀገራት ጋር በሚጋጩበት ወቅት የሚያደርሱት የሳይበር ጥቃት ነው ይላሉ።

# የግል የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ምንዛሪ በጥሬ ገንዘብ ለመሸጥም ሆነ ለመግዛት የሚሹ ደንበኞችን ፍላጎት ለማርካትና የጥቁር ገበያውን ለማዳከም እንደሚረዳ እየተነገረ ነው ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህሩ አጥላው ዓለሙ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፤ የብሔራዊ ባንክ የግል የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎችን መክፈት ለሚፈልጉ አካላት ፍቃድ መስጠቱ ነፃ ገበያን በመፍጠር ጥቁር ገበያው ሕጋዊ ፍቃድ አግኝቶ እንዲሠራ ማድረግን ያለመ ነው። ።

ማንኛውም አቅም ያለው ግለሰብ ቢሮ በመክፈት ዶላርንም ሆነ ሌሎች የውጭ መገበያያዎችን መሸጥና መለወጥ መቻሉ ግልጽ በሆነ መንገድ የውጭ ምንዛሪ እንዲንቀሳቀስና ባንኮችም በቀጥታ የውጭ ምንዛሪ እንዲያገኙ የሚያግዝ መሆኑንም ጠቁመዋል።

እንደ መምህር አጥላው ገለጻ፤ የውጭ ገንዘቦች በተለያየ ሁኔታ ውስጥ በሚመነዘሩበት ሁኔታም ኢኮኖሚውን መደገፋቸው አይቀሬ የነበረ ቢሆንም በሕጋዊ መንገድ ሲመጡ መንግሥት ከዘርፉ ማግኘት ያለበትን ገቢ እንዲያገኝ ያግዛል። ። እንዲሁም የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችም በድብቅ ከመሽሎክሎክ ይልቅ ሕጋዊ ሰውነት አግኝተው በነፃነት እንዲሠሩ ያደርጋል።

የጥቁር ገበያው ከመደበኛው የባንክ ምንዛሪ ተመን እጥፍ ሲመነዘር ኢኮኖሚውን በእጅጉ እየጎዳ እንደነበር የሚገልፁት አጥላው (ዶ/ር)፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን በማበረታታት የቴክኖሎጂ ሽግግርን፣ የመሠረተ ልማት እድገትንና የሥራ እድልን በማስፋት ለፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገት አስተዋፅዖ የሚያበረክት መሆኑ እሙን ቢሆንም የሠላም ጉዳይን ጨምሮ ለኢንቨስትመንት የሚሆን ምቹ ከባቢን መፍጠር ይፈልጋል ይላሉ።

የግል የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎች እንዲከፈቱ መፈቀዱ ትክክል ነው። ይህ አሠራር በኬንያ፣ ጅቡቲና ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። ። አብዛኛውን ጊዜ ጥቁር ገበያ የሚንሰራፋው በመደበኛው የውጭ ምንዛሪ ተመንና በገበያው ፍላጎት መካከል ከፍተኛ ልዩነት ሲፈጠር ነው።መገበያያዎች በጥቁር ገበያ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት የአደንዛዥ ዕፅና የተለያዩ ወንጀሎች እንዲሠሩ ሲደረግ የነበረበት ሁኔታ አሁን የሚቀንስ ይሆናል ነው የሚሉት።

መምህር አጥላው፤ አሠራሩ ከሀገር ውጭ መውጣት የሚፈልጉ ግለሰቦችም ሆነ ነጋዴዎች በቀላሉ የውጭ ምንዛሪዎች እንዲያገኙ ቢያደርግም በተቃራኒው በሀገር ውስጥ ለሚኖሩ ዜጎች ጉዳቱ ያመዝናል፤ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ሁኔታ ብር እየረከሰ በመሆኑ ሁሉም ዶላር የመያዝ ዝንባሌ እንዲያድርበት በማድረግ ብርን የበለጠ አቅም ሊያሳጣው ይችላል የሚል ስጋት እንዳላቸው ይገልፃሉ።

ፈቃድ መሰጠት መጀመሩ መልካም ቢሆንም ውሳኔው ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በቂ ተቀማጭ የውጭ ምንዛሪ መኖሩን ማረጋገጥና ኤክስፖርትን በማሳደግ የውጭ ምንዛሪ ምንጮችን ከመቼውም በበለጠ ማጠናከር እንደሚገባ የሚያነሱት አጥላው (ዶ/ር)፤ ነገር ግን በቂ የውጭ ምንዛሪ ምንጮች ሳይኖሩ ወደዚህ አሠራር መግባቱ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ይጠቁማሉ።

በዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ዳዊት ሀይሶ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ማንኛውንም የውጭ ምንዛሪ የሚፈልግ አካል እንደማንኛውም ቁስ ከገበያ ተደራድሮ መግዛት መቻሉ የውጭ ምንዛሪ ዋጋ በአቅርቦትና ፍላጎት እንዲወሰን በማድረግና ለገበያው ነፃነትን በመስጠት ተወዳዳሪነትን ያሳድጋል። እንዲሁም መንግሥት ከጉዳዩ መውጣቱ የጥቁር ገበያውንና የባንኮችን የውጭ ምንዛሪ ዋጋ ተቀራራቢ ያደርገዋል ይላሉ። ።

በተጨማሪም ለአላስፈላጊ ተግባር ዶላር የሚከማችበትንም ሁኔታ ያስወግዳል የሚሉት ዳዊት (ዶ/ር)፤ ሕጋዊ ያልሆኑ የግብይት ሠንሠለቶችን በመበጠስ የጥቁር ገበያው እንዲጠፋ ከማድረግ ባለፈ በጥቁር ገበያውና በሕጋዊ የምንዛሪ ገበያው መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥበብ እንደሚያግዝ ይገልጻሉ። ።

እንደ ምሑሩ ገለጻ፤ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሀገር ውስጥ ምርቶች ይልቅ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን የመሸመት ፍላጎቱ ከፍተኛ ነው። ነገር ግን ከዚህ በኋላ ምርቶችን ከውጭ ወደሀገር ውስጥ ለማስገባት ውድ የሚሆንበት አጋጣሚ የሚፈጠር በመሆኑ ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ያለው ፍላጎት እየቀነሰ ይመጣል። ። ይህም ሸማቹ ማኅበረሰብ ፊቱን ወደ ሀገር ውስጥ ምርቶች የሚያዞርበትን ዕድል ይፈጥራል።

እንዲሁም ምርቶችን ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ አካላት በሀገር ውስጥ እንዲያመርቱ አዎንታዊ ጫናን በማሳደር ከውጭ ምርቶችን ከማስገባት ይልቅ ወደውጭ ምርቶችን የመላክ ፍላጎት እያደገ እንዲሄድ እንደሚያግዝ የሚገልጹት ዳዊት (ዶ/ር)፤ ከዚህ ቀደም መንግሥት በኢኮኖሚ ሥርዓት ሳይሆን በሚሰጠው ድጎማ የብር አቅም ጠንካራ ሆኖ የቆየ ነበር ቢሆንም አሁን ላይ ይህንን ማስቀጠል የማይቻልበት ሁኔታ ላይ መደረሱን ያክላሉ።

አሠራሩ ተግባራዊ መደረጉ ብርን ከመገበያያነት ያወጣዋል የሚሉ ስጋቶች እንዲስተዋሉ ያደረገ መሆኑን ጠቁመው፣ ነገር ግን በኢትዮጵያ ውስጥ ብቸኛው የመገበያያ ገንዘብ ብር ብቻ ነው። በመንግሥት ተወስኖ እስካልተቀየረ ድረስ በብር መገበያየት ግዴታ ነው። በብር አልገበያይም የሚል አካልም በሕግ ተጠያቂ ይሆናል ሲሉ ስጋቱ ተገቢነት እንደሌለው ይገልፃሉ።

እንደ ዳዊት (ዶ/ር) ማብራሪያ፤ አሁን የሽግግር ጊዜ በመሆኑ ለአጭር ጊዜ የሚቆዩ የዋጋ ጭማሪዎች እና በነጋዴው ማኅበረሰብ ላይ ሸቀጦችን የማሸሽ ሁኔታዎች እየታዩ በመሆናቸው ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል።

መንግሥት ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኘውን ማኅበረሰብ ለመደገፍ በመሠረታዊ ሸቀጦች ላይ ድጎማ የሚያደርግ ከሆነም ሽግግሩ ጤናማ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ አቶ ማሞ ምሕረቱ፤ “የግል የውጭ ምንዛሪ ቢሮዎች እንዲከፈቱ የሥራ ፈቃድ መስጠታችን የኢትዮጵያን የፋይናንስ ዘርፍ ለውጭ ኢንቨስትመንት ለመክፈትና ዘርፉን በቀጣይ ዓመታት ከዓለም ምርጥ ተሞክሮዎችና አሠራሮች ጋር የተመጣጠነና ተወዳዳሪ ለማድረግ የጀመርነውን አዲስ ምዕራፍና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የጀመረውን ስትራቴጂካዊ ለውጥ ከግብ ለማድረስ በቁርጠኝነት መነሣሣቱን የሚያመለክት ነው” ማለታቸው የሚታወስ ነው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኦሊምፒክ ውጤታችን ቆም ብለን ማሰብ እንደሚገባን ያመላከተ ነው!

ኢትዮጵያ ከ1956ቱ የሜልቦርን ኦሊምፒክ ጀምሮ እስካሁኑ ፓሪስ 2024 ኦሊምፒክ ድረስ 15 ጊዜ በታላቁ መድረክ ተሳትፋለች፡፡ ከመጀመሪያ ተሳትፎዋ ሜልቦርን ኦሊምፒክ በስተቀር በ14ቱም የኦሊምፒክ ተሳትፎዋ ካለ ሜዳሊያ ተመልሳ አታውቅም፡፡ በዚህም 24 ወርቅ፣ 14 ብር እና 24 የነሐስ ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ በዓለም መድረክ ደማቅ ታሪክ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ተሰልፋ እናገኛታለን፡፡

በዚህ ዘመናትን በዘለቀው የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ተሳትፎ ከታሪካዊው አትሌት አበበ ቢቂላ የሮም ኦሊምፒክ የማራቶን የባዶ እግር ገድል አንስቶ እስካሁኑ ጀግና አትሌት ታምራት ቶላ የፓሪስ ኦሊምፒክ የማራቶን ድል ድረስ እልፍ ጀግኖች በዓለም አደባባይ የኢትዮጵያን ስም በወርቅ ቀለም ፅፈዋል፡፡

ከእንቁ አትሌቶቻችን ውጤት ይልቅ ከስፖርቱ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ጋር የሚነሱ ውዝግቦች ገንነው በታዩበት በዘንድሮው የፓሪስ 2024 ኦሊምፒክም አንድ ወርቅ በወንዶች ማራቶን እና ሦስት ብር በሴቶች ማራቶንና 800 ሜትር እንዲሁም በወንዶች 10 ሺህ ሜትር ሜዳሊያ ተመዝግቧል፡፡ አትሌቶቻችን በተሳተፉበት ውድድር ሁሉ ለሀገር የሚገባውን ተጋድሎ ፈጽመዋል፤ ለዚህም ሀገራዊ ምስጋናና ክብር ይገባቸዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን የፓሪስ ኦሊምፒክ ውጤት የኢትዮጵያ አትሌቲክስና ኦሊምፒክ መታመሙ የታየበት ሆናል፡፡

ከሳይንስ የተፋታና ተለምዷዊ የሆነ የአትሌቶች ምልመላ፣ መረጣና ሥልጠና ብዙ ርቀት እንደማይወስደን ከፓሪስ የኦሊምፒክ ውጤት በላይ ሊያስተምረን የሚችል አጋጣሚ የለም፡፡ በፍጹም ከሳይንስ ጋር የማይተዋወቅና ዘመኑን የማይመጥን የአሠለጣጠን ዘዴን መከተላችን ለውጤት መጥፋት ሌላኛው ምክንያት መሆኑን በርካታ ዘርፉ ባለሙያዎች እየተናገሩ ነው።

ለዚህ ማሳያው ደግሞ አትሌቶቻችን በታላቁ የኦሊምፒክ መድረክ ያሳዩት የአሯሯጥ ቴክኒክና ታክቲክ እንዲሁም የብቃት ደረጃ ነው። ተፈጥሯዊ አቅም ያላቸውን አትሌቶች ተቀብለን በምንከተለው ኋላ ቀር የምልመላ፣ መረጣና አሠለጣጠን ዘዴም ልንፈትሸው የሚገባ ጉዳይ ነው። ወቅቱን የሚመጥንና ወደ ሳይንሱ የሚያስጠጋን ስር ነቀል ለውጥ ያስፈልገናል።

የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ የውጤትም ሆነ የአስተዳደር ድክመት አደባባይ ላይ ተሰጥቷል። የኦሊምፒክ ውጤታችን ማሽቆልቆል የጀመረው ግን አሁን አይደለም፡፡ ከሦስት ኦሊምፒኮች አስቀድሞ ይስተዋሉ የነበሩ ችግሮች ተንከባለው አሁን ላይ ለታየው ቀውስ ዳርገውናል፡፡ ይህም የቀጣዩን ኦሊምፒክ ጉዟችንን ስጋት ውስጥ የከተተ አፋጣኝ መፍትሔ የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

ብርቅዬ አትሌቶቻችን አቅሙና ብቃቱ እያላቸው ውዝግብና ጭቅጭቅ በማያጣው አስተዳደራዊ እንቅፋት ተሸብበው የእኛ የሆኑ በርካታ ወርቆች ከእጃችን ወጥተዋል፡፡ እነዚህ ችግሮች በቀጣይ ኦሊምፒኮች እንዳይደገሙና ወደ ላቀ ውጤታማነታችን ለመመለስ አፋጣኝ መፍትሔ ማበጀት ለነገ የምንተወው የቤት ሥራ አይደለም፡፡ ለዚህም በዋናነት ከስፖርቱ አስተዳደራዊ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ብዙ ጉዳዮችን ፈትሾ ፈር ማስያዝ ያለብን አሁን ላይ ነው፡፡

በግለሰቦች ላይ ጣት ከመጠቆም ወጥተን ኢትዮጵያ በቀጣይ ወደ ተለመደው ውጤታማነት መመለስ የምትችልባቸው መፍትሔዎች ላይ ማተኮር ተገቢ ነው፡፡ ስፖርቱን በሚመሩ ግለሰቦች መለዋወጥ ሳይሆን በሥርዓት የሚመራ አስተሳሰብ መገንባት ያስፈልጋል፡፡

መንግሥት፣ ባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ፣ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን፣ ክለቦች፣ ማናጀሮች፣ አሠልጣኞች፣ አትሌቶች፣ ምሁራን፣ የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በጋራ ለለውጥ መሥራት አለባቸው፡፡ የዚህ ችግር ዋነኛ ተዋንያንም ተጠያቂ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

በተለይም በኦሊምፒክ ኮሚቴና በአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ስር ነቀል ለውጥ የግድ ነው፡፡ እየታዩ የሚገኙ አስተዳደራዊ ችግሮች ጥቂት ጀግኖች አትሌቶች በዓለም አቀፍ ውድድሮች በሚያስመዘግቧቸው ድሎች ተሸፋፍነው ማለፍ የለባቸውም፡፡ የነበሩንንና ያሉንን አትሌቶች አቅምና ክብር የሚመጥን ግልጽና ዘመኑን የዋጀ አሠራር መኖር አለበት፡፡

ተጠያቂነት በመጥፋቱ ኢትዮጵያ የምትታወቅባቸውን የአትሌቲክስ ውጤቶች እየተቀማች መቀጠል የለባትም፡፡ ኦሊምፒክ በመጣ ቁጥር ትርምስ የሚፈጥሩም ሆነ በሀገር ውጤት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲፈጠር የሚተጉ ግለሰቦችም ይሁኑ ቡድኖች እየቆመሩ ያሉት በሀገር ጥቅም እና ገጽታ ላይ መሆኑን ቆም ብለው ሊያስቡ ይገባል፡፡

በስፖርቱ ዘርፍ ውስጥ የሚገኙ አመራሮችም ሆኑ ባለሙያዎች ከሴረኝነት እና ከጥቅማ ጥቅም አነፍናፊነት እንዲሁም ከሀሜትና አሉባልታ ወጥተው የመርሕ ሰው መሆን አለባቸው፡፡ ካለፈው ስህተት ተምረን ስፖርቱ እውቀት፣ ክሒሎት፣ ሥነ-ምግባርና ኃላፊነት ባላቸው ሰዎች እንዲመራ ማድረግም ግድ ነው!


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# የፕሪቶሪያ ስምምነት መነሻና መድረሻው ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ተቋማትን ማክበር ነው!

## ወቅታዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የተሰጠ መግለጫ ሙሉ ቃል

የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ከሰሞኑ በተሻሻለው የምርጫ አዋጅ ቁጥር 1332/2016 አንቀጽ 2 (1) መሠረት ለሕወሓት የምዝገባ ምስክር ወረቀት መስጠቱን ገልጧል። መንግሥት ሕገ መንግሥታዊ ተቋማት በሕግና በተቋማዊ ነፃነት የሚወስኑትን ውሳኔ ይቀበላል። ያደንቃል። የለውጡ አንዱ ፍሬ ነውና።

ሕወሓት ሕጋዊ ሰውነቱን ያጣው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በፖለቲካ ፓርቲዎች የምዝገባ እና የሥነ ምግባር አዋጅ መሠረት ባስተላለፈው ውሳኔ መሆኑ ይታወሳል። ቦርዱ ፖርቲው በኃይል እና በአመፅ እንቅስቃሴ በመሳተፉ የፓርቲውን ምዝገባ እንዲሠረዝ በመወሰኑ፣ ሕወሓት ሕጋዊ ሰውነቱን ማጣቱ ይታወቃል። ይህ የምርጫ ቦርድ ውሳኔ የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕወሓትን ሽብርተኛ ብሎ ከመፈረጁ በፊት የተላለፈ እና ራሱን ችሎ የሚቆም፣ የራሱ የሕግ መሠረት ያለው ውሳኔ ነው።

የፕሪቶሪያ ስምምነት ሲፈጸም የፌዴራል መንግሥት በስምምነቱ የገባው ግዴታ የሕወሓት የሽብርተኝነት ፍረጃ እንዲነሣ ሂደቱን የማሣለጥ ኃላፊነት ነው (የስምምነቱ አንቀጽ 7 (2) (C))። የፌዴራል መንግሥት የሕወሓትን የሕግ ሰውነት እና የምዝገባ ጉዳይ በተመለከተ በፕሪቶሪያ ስምምነት ውስጥ የወሰደው የተለየ ኃላፊነት ወይም ግዴታ አልነበረም። እንዲሁም ሕወሓት በፕሪቶሪያ ስምምነት አንቀጽ 7 (1) (A) መሠረት የሀገሪቱን ሕገ መንግሥት፣ ሕጎች፣ የፌዴራል ተቋማትን እና ሌሎች ሕገ መንግሥታዊ ተቋማትን ሥልጣን የማክበር ግዴታ ገብቷል። ስለዚህ ሕወሓት የሀገሪቱን የፖለቲካ ፓርቲዎች የምዝገባ ሕግ እና የምርጫ ቦርድን ሥልጣን በማክበር የመሥራት ግዴታ እንዳለበት ግልጽ ነው።

ስለሆነም፣ ከፕሪቶሪያ ስምምነት አኳያም ሲታይ የሕወሓት የሕግ ሰውነት ጉዳይ አግባብነት ባለው ሕግ እና በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አሠራር መሠረት ብቻ እልባት ሊያገኝ የሚገባ ጉዳይ ነው። የፌዴራል መንግሥት በዚህ ረገድ ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና ከሕወሐት አመራሮች ጋር ተደጋጋሚ ምክክሮችን በማድረግ፣ ሕወሓት እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ሕጋዊ ዕውቅና እንዲኖረው ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል።

በዚህ ረገድ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አቋም፣ ሕወሓት ማንኛውም አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ በሚመሠረትበት ሥርዓት እና አግባብ መሠረት እንደ አዲስ ፖርቲ በመደራጀት ሊመዘገብ እና ዕውቅና ሊያገኝ ይችላል፣ ከዚህ ውጪ ግን ሕጋዊ ሰውነት ሊያገኝ የሚችልበት ሕጋዊ አሠራር የለም የሚል ነበር። በሕወሓት በኩል የነበረው አቋም ነባር እና እድሜ ጠገብ የፖለቲካ ድርጅት ስለሆንኩኝ እንደ አዲስ ፓርቲ ልመዘገብ አይገባም፣ ጉዳዩ የሕግ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ስለሆነ የተለየ የፖለቲካ ውሳኔ ይፈልጋል የሚል ነው።

እነዚህን የተለያዩ አቋሞች እና ፍላጎቶችን ከግምት በማስገባት፣ ሠላምን የማጽናት አስፈላጊነትን፣ እንዲሁም የዴሞክራሲ ተቋማትን ነፃነት እና ገለልተኝነት ባገናዘበ መልኩ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት የተሻለው መንገድ፣ ሕውሓትም ሆነ ሌሎች የትጥቅ እንቅስቃሴ ላይ ያሉ ቡድኖች ወደ ሕጋዊ መሥመር ሊመጡ የሚችሉበትን መንገድ የሚያመቻች የሕግ ማሻሻያ ማድረግ እንደሆነ በፌዴራል መንግሥት በኩል ታምኖበት አስፈላጊው የሕግ ማሻሻያ ለሕዝብ ተወካዮች ቀርቦ ፀድቋል።

በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ከተሻሻለ በኋላ፣ በተሻሻለው የአዋጁ ድንጋጌ መሠረት ሕወሓት የሕግ ሰውነት እንዲያገኝ ለማድረግ አስፈላጊ ወይም ቅድመ ሁኔታ የሆነው የሠላም ስምምነት መፈጸምን አስመልክቶ የፍትሕ ሚኒስቴር ለምርጫ ቦርድ ድብዳቤ ጽፏል።

በዚህም የሕወሓት ሕጋዊ ሰውነት ጉዳይ እልባት እንዲያገኝ ከመንግሥት በኩል ሊደረግ የሚችለው ሁሉ ተደርጓል። የፌዴራል መንግሥት ከግማሽ ርቀት በላይ ሄዶ፣ በፕሪቶሪያ ስምምነት መሠረት ከሚጠበቅበት እና ካለበት ግዴታ አልፎ ከምርጫ ቦርድ እና ከሕወሓት ጋር በጉዳዩ ላይ ተከታታይ ውይይቶች አድርጓል።

በተደረገው የሕግ ማሻሻያ መሠረት ምርጫ ቦርድ ሕወሓትን በመመዝገብ ድርጅቱ ሕጋዊ ሰውነት እና ዕውቅና እንዲኖረው ለቦርዱ የትብብር ጥያቄ አቅርቧል። ይህንንም ተከትሎ ሕወሓት ሕጋዊ ሰውነት እና ዕውቅና ለማግኘት የሚጠበቅበት የፓርቲ ሰነዶቹን ማለትም የፓርቲውን ፕሮግራም እና ሕገ ደንብ፣ እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ሰነዶችን ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በማቅረብ በተሻሻለው አዋጅ መሠረት ተመዝግቦ ሕጋዊ ሰውነት አግኝቷል።

ስለሆነም የምዝገባ እና የሕግ ሰውነትን ጉዳይ በዚህ በመቋጨት፤ የሁሉም ባለድርሻ አካል ርብርብ፣ ሠላምን በማጽናት፣ በመልሶ ግንባታ እና በልማት አጀንዳ ላይ ሊሆን ይገባል። አላስፈላጊ እና ሕዝብን የማይጠቅም፣ ትርጉም አልባ ንትርክን አስወግደን ለሕዝብ ረብ ያላቸው ጉልህ የሠላም እና የልማት አጀንዳዎች ላይ ልናተኩር ይገባል።

**ነሐሴ 6 ቀን 2016 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**
**የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት**

# ነፃ ሃሳብ

# የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ውጤታማ እንዲሆን የሰላም ሚና የማይተካ ነው

እስማኤል አረቦ

አሁን ላይ በዓለም ላይ 132 ሀገሮች በጦርነት እና በግጭት ውስጥ መሆናቸውን ፤ በ2023 ብቻ 17 ነጥብ 5 ትርሊዮን ዶላር ለጦርነት መዋሉን መረጃዎች ያመላክታሉ። በራሺያ እና በዩክሬን፣ በእስራኤል እና በፍልስጤም መካከል በየቀኑ በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ ለጦርነት እየዋለ ነው።

በራሺያ እና በዩክሬን፣ በእስራኤል እና በፍልስጤም መካከል የሚደረገውን ጦርነት ጨምሮ በሌሎችም ሀገሮች ባለው ጦርነት ሳቢያ 13 በመቶ የዓለም አጠቃላይ ምርት ለጦርነት እየዋለ እና ሰላም በመጥፋቱ ምክንያት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ እና ስደት ዓለምን እያስጨነቀ መሆኑንም መረጃዎች ያመለክታሉ።

የዓለም አካል የሆነችው ኢትዮጵያም በሰላም እጦት የተነሳ የምትፈልገውን ልማትና መረጋጋት ማምጣት አልቻለችም። ለሁለት ዓመታት ያህል በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በተካሄደው ጦርነት ከ20 ቢሊዮን ዶላር በላይ እንዳጣች በተደጋጋሚ ሲገለጽ ቆይቷል። ከዚያ በኋላ በአማራ እና በኦሮሚያ ክልል በተቀሰቀሱ ግጭቶች ሰላም ደፍርሷል፤ በርካቶች ተፈናቅለዋል፤ተሰደዋል፤ህይወታቸውን አጥተዋል።

እነዚህ የሰላም መደፍረሶች ደግሞ ሀገሪቱን ዋጋ አስከፍለዋታል፡፤ ሀገሪቱ የጀመረቻቸው አጓጊ ፕሮጀክቶች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ተዳርሰው እርካታ እንዳይፈጥሩ እንቅፋት ሆኗል። በምሥራቅ አፍሪካ ግዙፍ ኢኮኖሚ ባለቤት ብትሆንም ሰላሟ የተሟላ ባለመሆኑ የቱሪስቶችና የውጭ ባለሀብቶች መናኸሪያ እንዳትሆን የራሱን ጥላ አጥሎባታል። በዚህ ሁሉ ግጭትና አለመረጋጋት ውስጥም ሆና ሀገሪቱ በአፍሪካ ትልቅ ኢኮኖሚ ካላቸው ሀገራት መካከል በአምስተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች።

እንደ ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም መረጃ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ትልቅ ኢኮኖሚ ካላቸው ሀገራት መካከል አምስተኛ ደረጃን ይዛለች። ይህንንም ደረጃ ልትቆናጠጥ የቻለችው 205 ነጥብ1 ቢሊዮን ዶላር የሀገር ውስጥ ጠቅላላ ገቢ(GDP) በማስመዝገብ ሲሆን፤ ይህም ሀገሪቱ በኢኮኖሚ ግስጋሴ ውስጥ እንድትገኝ አመላካች ነው።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ከደቡብ አፍሪካ ፣ከግብፅ፣ከአልጄሪያ እና ከናይጄሪያ ቀጥሎ በአምስተኛ ደረጃ ተጠቃሽ ነች። ኢኮኖሚዋም በቀጣይ የተሻለ እድገት ሊያስመዘግብ እንደሚችል ብዙ ተስፋ የተጣለበት ጭምር ነው። መንግሥትም የተመዘገበውን ውጤት የተሟላ እና ዘላቂ ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ ማሻሻያዎች እየወሰደ ነው።

ከእነዚህ ውስጥ በአይነቱ የተለየ እና እምርታዊ ለውጥ ያመጣል ተብሎ የታመነበትን አዲስ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥርዓት ተግባራዊ አድርጓል። የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አካል ሲሆን፤ ዋና ግቡ ቀጣይነት ያለው፣ መሠረተ ሰፊና ሁሉን አሳታፊ የኢኮኖሚ ዕድገት መኖሩን ማረጋገጥ ነው።

የማይክሮ ማሻሻያው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓቱ፤የውጭ ምንዛሪ ተመን በባንኮችና በደንበኞቻቸው መካከል ወደሚወስንበት የገበያ ሥርዓት የሚያሸጋግር ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሚና፣ ገበያውን በማረጋጋት ላይ ያተኮረ እንዲሆን የሚያደርግ፤ የውጭ ምንዛሪን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የማስተላለፍ ግዴታን ያስቀረ ነው።

ላኪዎችና ንግድ ባንኮች ያፈሩትን የውጭ ምንዛሪ ለራሳቸው ማስቀረት እንደሚችሉ የሚደነግግ ፤ለግሉ ዘርፍ የሚሰጠውን የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት በእጅጉ የሚያሻሽል ፣ምርቶችን ወደ ውጭ የሚልኩ ነጋዴዎች ካፈሩት የውጭ ምንዛሪ ገቢ ለራሳቸው ያስቀሩት የነበረው 40 በመቶ ወደ 50 በመቶ ከፍ የሚያደርግ ነው። ይህም ላኪዎች የበለጠ ተበረታትተው እንዲሰሩ የተሻለ የውጭ ምንዛሬ እንዲያመጡ በር የሚከፍት ነው።

ከውጭ የሚላክ ሐዋላን፣ ደመወዝን፤ የኪራይ ገቢን እና ሌሎች ገቢዎችን በውጭ ምንዛሪ ለመክፈል የሚያስችል የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦችን መክፈት የሚያስችል፣ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች ተጠቅመው የውጭ አገልግሎት ክፍያዎችን እንዲፈጽሙ የሚፈቅድ ነው። ይህም በሀገሪቱ የተሻለ የውጭ ምንዛሬ እንቅስቃሴ እንዲኖር ከማስቻል ባለፈ እጥረቱንም እንደሚያቃልል ይታመናል።

የውጭ ኢንቨስተሮች በኢትዮጵያ ሰነድ መዋእለ ንዋይ ገበያ (Ethiopian Securities Exchange) እንዲሳተፉ የሚፈቅድ፤ በልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች ውስጥ የሚሠሩ ኩባንያዎች የውጭ ምንዛሪ ገቢያቸውን ሙሉ በሙሉ ለራሳቸው መያዝን ጨምሮ ልዩ የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀም መብት የሚሰጣቸው ነው።

በተመሳሳይም ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ ሀገራት የሚጓዙ ወይም ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ መንገደኞችን ሊይዙ በሚገባ የውጭ ምንዛሪ ጥሬ ገንዘብ መጠን ላይ ተጥለው የነበሩ የተለያዩ ጥብቅ ደንቦች እንዲላሉ አድርጓል።እነዚህ እርምጃዎች የዶላር እና ሌሎች ዓለም አቀፍ ገንዘብ ያላቸው ባለሀብቶች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡና ገንዘባቸውን በተለያዩ ልማት ስራዎች እንዲያፈሱ ዕድል የሚሰጥ፤ ቀጣዩን የኢትዮጵያን የዕድገት ደረጃና ከቀረው የዓለም ሀገራት ጋር ያላትን እያደገ የመጣውን ትስስር ለማጠናከር የሚረዳ ነው።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ወደ ሙሉ ትግበራ የገባችበት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥርዓት የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲያድግና የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲኖር ያስችላል።ለዚህ ግን ከሁሉም በላይ የሰላም ጉዳይ ወሳኝ እንደሆነ ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም ። የውጭ ባለሀብቶችም ሆኑ ቱሪስቶች ወደ ሀገር ውስጥ መጥተው ሀገርን ተጠቃሚ ለማድረግ ሰላም ለነገ የሚባል የቤት ሥራ አይደለም።

ቀደም ባሉት ጊዜያት ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ተነጻጻሪ ሆነ ሰላም ካላቸው ሀገራት አንዷ ብትሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ሰላሟን የሚያደፈርሱ ክስተቶች እየተስተዋሉ ናቸው። በሀገሪቱ ፍላጎታቸውን በነፍጥ ማሳካት የሚፈልጉ ቡድኖች እየተበራከቱ መጥተዋል። ከውይይት ይልቅ ነፍጥ ማንሳት የሚቀናቸውና ሰላም ወዳዱን ሕዝብ የሚረብሹ፣ አብሮነቱን የሚያውኩ ፣የኢትዮጵያን መረጋጋትና ሉአላዊነት የሚገዳደሩ ቡድኖች እዚህም እዚያም አቆጥቁጠዋል።

እነዚህ ወገኖች በሚፈጥሩት ሁከትና ብጥብጥም ልማት ተደናቅፏል፤ የሰዎች ወጥቶ መግባት ተስተጓጉሏል፤አለፍ ሲልም የሀገር ህልውናም አደጋ ላይ ወድቋል። ሀገር በሰላም ውላ እንድታድርና እድገትና ብልጽግና እንዲረጋገጥ እነዚህን የሰላም ጸሮች በጋራ መመከት ያስፈልጋል።

> **ከውጭ የሚላክ ሐዋላን ፣ ደመወዝን፤ የኪራይ ገቢን እና ሌሎች ገቢዎችን በውጭ ምንዛሪ ለመክፈል የሚያስችል የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦችን መክፈት የሚያስችል ፣እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦች ተጠቅመው የውጭ አገልግሎት ክፍያዎችን እንዲፈጽሙ የሚፈቅድ ነው፡፡ ይህም በሀገሪቱ የተሻለ የውጭ ምንዛሬ እንቅስቃሴ እንዲኖር ከማስቻል ባለፈ እጥረቱንም እንደሚያቃልል ይታመናል**

መንግሥት በሀገሪቱ እጣ ፈንታ ላይ የተጋረጡ በርካታ ችግሮችን በማስወገድ ብልፅግናን ለማምጣጥ በሁለንተናዊ መልኩ እየተንቀሳቀሰ ነው ።ለዘመናት የተከማቹ ኢኮኖሚ ስንክሳሮችን ለማስወገድም ወደ አዲስ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ማዕቀፍ ገብታለች። ይህ አዲስ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በተሟላ መልኩ ውጤት እንዲያመጣ ሰላም ያለውን የጎላ ድርሻ ሁሉም ዜጋ ሊያስተውለው ይገባል።

የሀገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በሙሉ ለመነጋገርና ለመደማመጥ ጊዜ መስጠት አለባቸው። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የኑሮ ውድነት አለ። በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ከተካሄዱ ጦርነቶችና ግጭቶች ገና አላገገምንም ፤ሥራ አጥነት አሁንም አሳሳቢ ነው፤አሁንም ከድህነት ያልወጣ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ አለ፤በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ድርቅ ደጋግሞ እያጠቃን ነው።

እነዚህን ችግሮች ለመሻገርና የተሻለች ኢትዮጵያን ለመገንባት ሰላም ወሳኝ ነው። ሰላም ለማምጣት ደግሞ በየጊዜው የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመሳሪያ ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ ቁጭ ብሎ የመነጋገር እና የመወያየት ባህል ማዳበር ይገባል። እንደ ሀገር እድገትና ብልጽግንና ማረጋገጥ የሚቻለውና የታለሙ ሀገራዊ ዕቅዶችንም በተሟላ መልኩ መተግበር የሚቻለው ሰላም ሲኖር ነው። ሰላም የሁሉም ነገር መሰረት ነው። እንኳን እድገትና ብልጽግና ለማረጋጥ በቀላሉ የእለት እንጀራን ለማሟላት ሰላም ያስፈልጋል።

ዜጎች ለሰላም ትኩረት መስጠት አለባቸው። በተራዘመ የሰላም እጦት ሳቢያ ሀገሪቱ ከእድገት እና ልማት ወደ ኋላ ቀርታለች።ትናንት በእድገት ተመጣጣኝ የነበሩ ሀገራት ዛሬ በእድገትና በስልጣኔ ገስግሰዋል፤የሕዝባቸውን ህይወት አሻሽለዋል፤በዓለም ላይም ተደማጭ ሆነዋል።

ኢትዮጵያውያን ከንግግር እና ውይይት ይልቅ የሃሳብ ልዩነቶቻቸውን በጠመንጃ እና በኃይል ለመፍታት በመሞከራቸው እድገታቸው ቁልቁል ከመሆኑም በሻገር በዓለም ላይ ተደማጭነታቸው እያሽቆለቆለ መጥቷል። በዓለም ላይ በተረጂነት ከሚታወቁ ሀገራት ግንባር ቀደሙን ቦታ ለመያዝ በቅተዋል።

ይህ ሀገርን እና ሕዝብን የጎዳ አካሄድ አንድ ቦታ መቆም አለበት። ኢትዮጵያውያን ጦርነትና ግጭት በቃን ሊሉ ይገባል። ችግሮችን በአፈሙዝና ነፍጥ በማንሳት ለመፍታት መሞከር ዋጋ እንዳስከፈለን ሊረዱ ይገባል። በየስርቻው ነፍጥ እያነሱ እኔ አውቅልሃለሁ የሚሉ ቡድኖች ሊያወግዛቸው ይገባል።

ዛሬ ዘመኑ ተለውጧል። ዓለም በሳይንስና በቴክኖሎጂ በሚራቀቅበት ወቅት እኛ ዛሬም ከመንደር ሳንወጣ ነፍጥ አንግበን ጫካ ለጫካ መዞር ሊያሳፍረን ይገባል። በመረጥነው ግጭትና ጦርነት የዓለም ጭራ መሆናችን ሊያንገበግበን ይገባል። ክብር የሌለንና እርዳታ ጠባቂዎች መሆናችን ሊያሳፍረንና ሊያሸማቅቀን ይገባል።

ኢትዮጵያ ዛሬ ከዓለም ተርታ ለመሰለፍ በመንደርደር ላይ ትገኛለች። ዓለም ከደረሰበት የእድገት ደረጃ ለመድረስ ለሰው ሰራሽ አስተውሎት (በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ) ትኩረት ሰጥታለች። ቴክኖሎጂ ወሳኙ መንገድ መሆኑን በመረዳት ወጣቶቿን በስልጠና እና በፈጠራ በስፋት በመሳተፍ ላይ ትገኛለች።

አልፎ ተርፎም ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት እንዲጎለብት የውጭ ባለሀብቶች በስፋት እንዲሳተፉ በሯን ክፍት አድርጋለች።በችርቻሮና በጅምላ ንግድ ሳይቀር የውጭ ባለሀብቶች በስፋት እንዲሳተፉ አውጃለች። የውጭ ባንኮች እንዲገቡና እንዲሰሩም ጥሪ አድርጋለች።ዶላር በገበያ ዋጋ እንዲገዛና እንዲሸጥ በመወሰንም ገበያ መር ኢኮኖሚን አውጃ ሙሉ ለሙሉ የለውጥ ምዕራፍ ውስጥ ገብታለች።

እነዚህ ውሳኔዎቿ ደግሞ የውጭ ባለሀብቶች በስፋት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ሰፊ እድል ይሰጣሉ። በዚህም የሥራ እድል እንዲከፈትና ሥራ እጥነት እንዲቀንስ የጎላ ድርሻ ይኖረዋል። የሀገሪቱን የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ የቱሪዝም ሀብቶች ለመጎብኘት የሚመኙ ብዙዎች ናቸው ።

ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን ሰላም ሲኖር ነው። በተለይም ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ወደ ሙሉ ትግበራ የገባችበት የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያው በርካታ ቱሪስቶችን እና የውጭ ባለሀብቶችን በእጅጉ የሚስብ ነው።ይህ እንዲሆን ደግሞ ሀገሪቱ በሰላም ውላ ልታድር ይገባል።ለዚህ ደግሞ የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት ትልቅ ነው።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## መልካም እድል ይዞ የመጣው ‹‹የኢትዮጵያ ኮደርስ ኢንሼቲቭ››

**ወርቅነሽ ደምሰው**

አሁን ባለንበት ዘመን ዲጂታል ቴክኖሎጂ ለሰው ልጅ አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ እንደምግብ፣ መጠለያና ልብስ ሁሉ መሠረታዊ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል። ከቴክኖሎጂው ውጪ መሆን የማይታሰብበትና የማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል።

ያደጉ ሀገራት በዲጂታል ቴክኖሎጂው ብዙ ርቀት ተጉዘዋል፤ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ታዳጊ ሀገራትም የዚህን ቴክኖሎጂ ፋይዳ በሚገባ በመገንዘብ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተደራሽነትን ለማስፋትና በቴክኖሎጂው ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ ይገኛሉ። ለእዚህም በዘርፉ የሰለጠነና ብቁ የሰው ኃይል እንዲኖራቸው የማድረጉን ስራ ቅድሚያ ሰጥተውታል።

ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን አዘጋጅታ በመተግበር ላይ በምትገኘው ኢትዮጵያም ዲጂታል ምህዳሩን በማስፋፋት ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆን ለማደረግ ዘርፉ ብዙ ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው። ይህን ተከትሎ እየተከናወኑ ከሚገኙ ተግባሮች መካከል ክፍያዎች፣ ግብይቶች እንዲሁም ጉዳዩ በዲጂታል ቴክኖሎጂ እንዲፈጸም እየተደረገ ያለበትን ሁኔታ ለእዚህ በአብነት መጥቀስ ይቻላል፤ በዲጂታል ቴክኖሎጂ በትሪሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ማዘዋወር እየተቻለ ነው፤ እንግልትና ወጪን በመቀነስ ጊዜ መቆጠበ ተችሏል። አገልግሎቶችን ማቀላጠፍ፣ ማዘመን፣ ወዘተ የሚያስችሉ መተግበሪያዎችን የማልማቱ ስራም ተስፋፍቷል።

በዲጂታል ቴክኖሎጂው በተለይ በመተግበሪያ ልማቱና በመሳሰሉት የበለጠ ልቆ ለመገኘት ዜጎችን በተለይ ወጣቶችን በኮዲንግ ላይ ማሰልጠን ወሳኝ መሆኑ ይታመናል።

ኮዲንግ ሰዎች ከሚጠቀሙበት ስልክም ሆነ ኮምፒውተር ጋር ለመግባባት የሚያግዛቸው የኮምፒውተር ቋንቋ ስለመሆኑ የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ። በአሁኑ ወቅትም የኮምፒውተር ቋንቋ ፋይዳው ብዙ እንደሆነ ሆኗል። በተለይ ወጣቶች በዚህ ቴክኖሎጂ ልቀው እንዲገኙ ለማድረግ ኮዲንግ ወሳኝ መሆኑ ነው።

በኢትዮጵያም ወጣቶችን በዚሁ ቴክኖሎጂ ለማሰልጠን የሚያስችል ምህዳር ተፈጥሯል። በቅርቡም ከዩናይትድ አረብ ኤሜሬት ጋር ወጣቶችን በኮዲንግ ለማሰልጠን የሚያስችል ስምምነት መፈረሙ ይታወሳል። በዚህ ስልጠና አምስት ሚሊዮን ዜጎች ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ይህንን ‹የኢትዮጵያ ኮደርስ ኢንሼቲቭ› ስልጠና በቅርቡ በይፋ አስጀምረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚሁ ወቅት እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ አምስት ሚሊዮን ኮደሮች ፈጠረች ማለት በሀገር ውስጥና በውጭ በቀላሉ ሥራ ሊያገኙ የሚችሉ ወይም ሥራ ሊፈጥሩ የሚችሉ አልያም ኩባንያ ሊፈጥሩ የሚችሉ ዜጎችን ፈጠረች ማለት ነው። ኮዲንግ ነገ ልክ እንደ ጎማ መቀየር ተራ ልምምድ ይሆናል። ያኔ ልጆቻችን ግራ እንዳይገባቸው ከወዲሁ መልካም ዘር ሊዘራባቸው ይገባል ሲሉም አስገንዝበዋል። ወጣቶች የተመሰከረላቸው/ ሰርቲፋይድ/፤ የሚፈጥሩ፣ የሚተጋገዙና ችግሮችን ለመፍታት የሚጥሩ፣ የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን ለማድረግ የጀገኑ እንዲሆኑም አሳስበዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ(ዶ/ር) በበኩላቸው አምስት ሚሊዮን ወጣቶች በኦንላይን እንደሚሰለጥኑ ጠቅሰው፤ ስልጠናው ከሚፈጥረው መልካም እድል ባለፈ የመሰረተ ልማት ውስንነት እና የዲጂታል መሳሪያዎች ተደራሽነት ስለመኖሩ አመላክተዋል። ወጣቶች ለሀገራቸው የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን አንቀሳቃሽ ኃይል መሆናቸውን ተገንዘበው ለኢንሼቲቩ ለስኬታማነት መረባረብ እንደሚገባቸው አስገንዝበዋል።

አቶ ፊሊክስ ኢቴሳ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሶፍትዌር ኢንጂነሪንግ ባለሙያ ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት፤ ኮዲንግ /ፕሮግራሚንግ/ስንል የሰው ልጅ ከማሽን ጋር የሚግባባበት ሥርዓት ነው። ይህም ኮምፒውተር እንዲሰራ የሚፈለገው ሥራ የሚታዘዝበት ሥርዓት ነው። ይህ ሥርዓት /ሲስተም/ ከሚሰጠው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ መካከል የመጀመሪያው የሰው ልጆችን ሥራ ማቀላጠፍ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ሰዎች ካሉበት ሆነው እርስ በእርስ እንዲገናኙ እንዲግባቡ ማድረግ ነው።

በኢትዮጵያ አምስት ሚሊዮን ወጣቶች በኮዲንግ እንዲሰለጥኑ ማድረግ ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታው አለው ሲሉም አስታውቀዋል። ምክንያቱም ዓለም ወደ ግሎባላይዜሽን እየገባች ባለችበት በዚህ ዘመን እኛ ከዲጂታል ቴክኖሎጂ ርቀን መኖር አንችልም። ዲጂታል ቴክኖሎጂ ያስፈልገናል ሲሉም ጠቅሰው፤ በየትኛውም የሥራ ዘርፍ ላይ ያለ ሰው ኮምፒውተር መጠቀም አለበት ብለዋል። በማሽን ወይም በኮምፒውተር በመታገዝ ብዙ ሥራዎች መስራት፣ ጊዜ፣ ገንዘብ እና ወጪን መቆጠብ የሚያስችል ቀላል የመግባቢያ ዘዴ መሆኑንም አስታውቀዋል።

በኮዲንግ መስልጠን ለኢትዮጵያ በተለይም ለወጣቶች የሚያበረክተው አስተዋጽኦ የላቀ ስለመሆኑ ያስረዱት አቶ ፊሊክስ፤ ለአብነት አንድ ታካሚን ለመመርመር አንድ ሰዓት የሚፈጅ ከሆነ፤ አንድ ቴክኖሎጂ ስንጠቀም ግን በአንድ ሰዓት ውስጥ አንድ ሺ ታካሚዎችን መርምሮ ወዲያውኑ ውጤቱን በማውጣት የሰውን ሕይወት ማዳን ይቻላል። በተለመደው መልኩ/ በማንዋል/ ሲሰራ ደግሞ አንድ ሰው ለማከም አሥር ሰው የሚታይበትን ሰዓት ሊወሰድ ይችላል።በዚህም ሰዎች ቴክኖሎጂን ተጠቅመው በኦንላይን ውጤታቸውን ማየት ይችላሉ። ከዚያም በላይ የሆኑ ብዙ ሥራዎች ሊሰሩበትና ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ይህ ስልጠና ለኢትዮጵያውያን መሰጠቱ በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ስልጠናውን የሚሰጠው ድርጅትም ፕሮፌሽናል የሆነ ትልቅ ድርጅት ነው። ስልጠናውን መውሰድ ጥሩ እውቀት እንዲገኝ ያስችላል። ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያውያንም ጥሩ አጋጣሚ ነው። ሊሰጡ የታሰቡ ኮርሶችም ቢሆኑ በጣም ውድ የሆኑና በግል ለመማር ቢፈለግ በነጻ የማይገኙ ናቸው። ‹‹እነዚህን ኮርሶች መውሰዳችን ለኛ በጣም ትልቅ እድል ነው ብዬ እገምታለሁ›› ሲሉም አብራርተዋል።

ሌላው ደግሞ ቴክኖሎጂ መጠቀም ብዙ ችግሮች ለመፍታት ይጠቅመናል። ቴክኖሎጂ አስፈላጊ ብቻ አይደለም። ልክ ለሰው ልጅ እንደሚያስፈልጉ እንደ ምግብ፣ መጠለያና ልብስ ያሉ መሠረታዊ ነገሮች ቴክኖሎጂ አንዱ መሠረታዊ ነገር ነው። ምክንያቱ ከቴክኖሎጂ ርቆ መኖር ሆኖ ከቴክኖሎጂ ውጭ መሆን የማይቻልበት ጊዜ እየደረስን ነው ብለዋል ።

ስልጠናው አምስት ሚሊዮን ወጣቶች ሊወስዱት የሚገባ መልካም እድል ነው። አንድ ሀገር ላይ አንድ ሰው የመፍጠር ችሎታ ካለውና አዲስ ነገር መፍጠር ከጀመረ ኩባንያ ማቋቋም፣ በገቢና ወጪ ኢምፖርት ኤክስፖርት/ ንግድ ውስጥም መግባት ይችላል።

በኮዲንግ ሰልጥኖ መገኘት ወደውጭ ኤክስፖርት ከሚደረጉ ሀብቶች በበለጠ የሰለጠነ የሰው ኃይል ወደ ውጭ መላክ ያስችላል። የሰለጠነ የሰው ኃይል ሲላክ አዲስ ቴክኖሎጂ፣ አዲስ እውቀትና ፈጠራም ለሀገሪቱ ይዞ ይመጣል። በተለይ በቴክኖሎጂ የታገዘ አንድ ብቻ ሳይሆን ሁለት እና ከዚያ በላይ እውቀት ይዞ መገኘት ከዓለም እኩል እንዲሆኑ ይረዳል ሲሉም ጠቅሰው፤ የተጀመረው ኢንሼቲቭ ጥሩ ጅምር መሆኑንና እድሉን መጠቀም እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

አቶ ፊሊክስ እንዳስታወቁት፤ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም ብዙ ነገሮች ያስፈልጋሉ። አንድ ሰው ለመማር ኮምፒውተርና መሰል የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ያስፈልጉታል። እነዚህ መሳሪያዎች በቀላሉ የሚገኙባቸው ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር ይገባል። ለዚህ ደግሞ ሁነኛ የዲጂታል ፖሊሲ መኖር አለበት።

‹‹እንደዚህ አይነት እድሎች በመንግሥት በኩል ሲመጡ ወርቃማ እድል እንደሆኑ ይቆጠራሉ›› ያሉት አቶ ፊሊክስ፤ ህብረተሰቡ እድሎቹን በመጠቀም ቴክኖሎጂውን ለጥሩ ተግባር በማዋል በጤና፣ በግብርና፣ በትምህርት እና በሁሉም በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካዊ ዘርፎች ላይ ያሉ ችግሮች መፍታት ይጠበቅብናል ሲሉ ያስረዳሉ።

እንደ አቶ ፊሊክስ ማብራሪያ፤ በቀጣይም ኮዲንግ ብቻ ሳይሆን ከኮዲንግ በተጨማሪ ሳይንሱንም መማርና

> **በኮዲንግ ሰልጥኖና መገኘት ወደውጭ ኤክስፖርት ከሚደረጉ ሀብቶች በበለጠ የሰለጠነ የሰው ኃይል ወደ ውጭ መላክ ያስችሳል፡፡ የሰለጠነ የሰው ኃይል ሲላክ አዲስ ቴክኖሎጂ፣ አዲስ እውቀትና ፈጠራም ለሀገሪቱ ይዞ ይመጣል**

ማወቅ ያስፈልጋል። እነዚህን ነገሮች ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይገባል። ግንዛቤ መፍጠር ላይም መስራትን ይጠይቃል። ኅብረተሰቡ በየጊዜው የሚመጡ እድሎች ጥቅም ምንድነው የሚለውን ማወቅ አለበት፤ እድሉ ሊያመልጠው አይገባም። ምክንያቱም ለዚህ ኮርስ የወጣበት ፋይናንስም ቀላል የሚባል አይደለም። በተለይ ወጣቶች እድሉ ሊያልፋቸው አይገባም እድሉን ተጠቅመው ተምረው የራሳቸውን ስራ መፍጠር ይጠበቅባቸዋል።

‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ የለም ከተባለ እንኳን በሌሎች ሀገራት ሥራ የማግኘት እድል ይፈጥረላቸዋል። ኬንያ፣ ዩጋንዳ እና ሕንድ በመሄድ መስራት ይችላሉ። በኢትዮጵያም ሥራ ፈጥረው መስራት ይቻላሉ›› ይላሉ።

በመንግሥት በኩል መሻሻል ያለባቸው ፖሊሲዎች በየጊዜው እንዲያሻሽሉ ማድረግ እንደሚገባም ጠቁመው፣ ገበያው ዲጂታል እንዲሆን በማድረግ የሥራ እድሎችን ማስፋት እንደሚጠበቅ ይናገራሉ። ይህ ደግሞ በቀላሉ የማይገኙ ሀብቶች እንዲገኙ ያደርጋል። በተለይ በትምህርት በኩል ኢትዮጵያ ውስጥ የማናገኛቸውን የትምህርት አይነቶች በኦንላይን ማግኘት ከማስቻልም ባለፈ የሥራ እድሎች በጣም እየሰፉ ነው። ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በመኖራቸውም ብዙ ፕሮጀክቶች ተቀርጸው ተግባራዊ ይደረጋሉ ብለዋል።

ቴክኖሎጂ ባህላዊና ማህበራዊ ተጽዕኖዎችም አሉት። ነገር ግን ቴክኖሎጂ ስናመጣና ተግባራዊ ስናደርግ ባህልና መሰል ነገሮችን ያገናዘበ መሆን አለበት። ምክንያቱም ቴክኖሎጂ ብቻ አምጥተን ተግባራዊ ማድረግ ሲያስፈልግ ከነባራዊ ሁኔታው ጋር በማጣጣም ህብረተሰቡ ሊጠቀምበት በሚችል መልኩ ሊሰራበት ይገባል።

‹‹ምን ያህሉ ነው ስለቴክኖሎጂ ጥቅም የሚያውቀው፤ ምን ያህሉስ ኮምፒውተር አለው የሚሉትና የመሳሰሉትን ሳናጠና ሁሉን ነገሮች ኦንላይን ስናደርግ ከማንዋል አሰራር የበለጠ ዲጂታል ሲስተም ቀውስ ይፈጠራል›› ሲሉ ያስገነዘቡት አቶ ፊሊክስ፣ እነዚህና መሰል ሁኔታዎችን አሁን ከወጡ ፕሮግራሞች ጋር አስተሳስሮ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በማስጨበጥ ላይ መስራት እንደሚያስፈልግ ጠቅሰዋል። ይህ ደግሞ ከመንግሥት ብቻ የሚጠበቅ ኃላፊነት እንዳልሆነም ተናግረው፤ ማህበረሰቡ ሊሳተፍበት እንደሚገባ አስታውቀዋል።

በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የብሔራዊ የኔትወርክ ማሳለጫ ፕሮጀክት መሪ አቶ ዳንኤል አድነው በበኩላቸው፤ አሁን እንደ ሀገር ሁሉንም ነገር ከውጭ እያወረድን ነው የምንጠቀመው ይላሉ። ዲጂታላይዜሽን በራሱ ኮዲንግን / ፕሮግራሚንግ/ ይጠይቃል ሲሉም ጠቅሰው፤ ኮዲንግ ለማድረግ ደግሞ የሰለጠነ የሰው ኃይል የምናስመጣው ከውጭ ነው ይላሉ። በኮዲንግ የተሰራውን ሥራ በራሱ ለማስተካከል የኮዲንግ እውቀት እንደሚያስፈልግ ተናግረው፤ በተለያዩ ዘርፎች ላይ ኮድ የሚያደርግ የሰው ኃይል/ወጣቶች/ እንዲኖር ማድረግ የግድ መሆኑን አመልክተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ መረጃዎችን ኮድ በማድረግ አገልግሎቱ አንላይን እንዲሆን ሲፈለግ ቀድሞ ከነበረው የተለመደ አሠራር አውቶሚት የሚደረገው በኮዲንግ ነው። በዚህ ብዙ የሰለጠነ የሰው ኃይል ሲኖር ብዙ ሰዎች የሥራ እድል እንዲፈጠርላቸውና ሥራውም በፍጥነትና በቅልጥፍና እንዲሰራ ያግዛል። ብዙ ኮድ የሚያደርጉ ወጣቶች ሲኖሩ ሁሉም ዘርፍ ላይ ያለውን መረጃ ከማንዋል አሠራር ዲጂታላይዝ በማድረግ አገልግሎቱን በኦንላይን በፍጥነት ማግኘት ያስችላል። የሥራ ፍጥነት እንዲኖር ማድረግ ብቻም ሳይሆን ኢኮኖሚ እንዲያድግም ያደርጋል።

በሁሉም ዘርፍ ኮዲንግን/ፕሮግራሚንግ/ ያላካተተ አውቶሜሽን የለም የሚሉት አቶ ዳንኤል፤ ዲጂታይዝድ ማድረግ በሁሉም ዘርፍ አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻል። ለአብነት በግብርና ዘርፍ የእርጥበት መጠንን ለመለካት ቢፈለግ መሳሪያ ማስቀመጥ በተፈለገ ጊዜ መለካት ይቻላል። ያንን ለማወቅ ቦታው ድረስ መሄድ ሳያስፈልግ ኮድ ተደርጎ ከተሰራ ውጤቱን ባሉበት ቦታ ሆኖ ማግኘት ያስችላል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ዳንኤል ማብራሪያ፤ የኢትዮጵያ ኮደርስ ኢንሼቲቭ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተነደፈ ፕሮግራም ነው። በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በኩል ይሄ ሥራ እንዲሰራ ምን ያስፈልጋል የሚለውን ማየት ያስፈልጋል። ለምሳሌ አንድ ኮደር ለማሰልጠን የሚያስፈልጉ ነገሮች አሉ። ኮደሩ በሀገር ውስጥ ነው ወይስ ውጭ ሀገር ነው የሚሰለጥነው። በሀገር ውስጥ የሚሰለጥን ከሆነ የሚያሰለጥን የሰው ኃይል አለ ወይስ የለም የሚሉት በደንብ መታየት አለባቸው።

አምስት ሚሊዮን ኮደሮችን ለማስልጠን ከሚያስፈልጉት መካከል የፋይናንስ አቅምና መሳሪያዎች ይገኙበታል። መሳሪያዎች ስንል ኮምፒውተር፣ የተሰራው ኮዲንግ አርካይቭ የሚደረግበት የኦንላይንና የክላውድ አገልግሎቶች ሶፍት ዌርም እጅግ ያስፈልጋሉ።

እነዚህን በማሟላት ረገድ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ኦፕሬቲንግ ሲስተም ሀገር ውስጥ እየሰራ በመሆኑ ኦፕሬቲንግ ሲስተም የሚወጣው ወጪ ማስቀረት እንችላለን። ኮደሮቹ ኮድ የሚያደርጉባቸው የተለያዩ የፕሮግራሚንግ ቋንቋዎችን እና ክላውድ ሲስተምም ጨምሮ ብዙ የሚያስፈልጉ ነገሮች በሀገር ውስጥ ማቅረብ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን አቶ ዳንኤል አስታውቀዋል።

‹‹ይህን እድል ሳንጠቀምበት ቆይተናል። እንደ ህንድ፣ ኬንያ ያሉ ሀገራት ብዙ ተጠቅመውበታል፤ እኛም ብዙ ልንጠቀምበት የሚገባበት እድል ነው ›› ያሉት አቶ ዳንኤል፤ ይህን እድል ወደ ተግባር ቀይርን ከተጠቀምንበት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ትልቅ እድገት ያስገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ ትንታኔ

# ማሻሻያው የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የደም ዝውውር ያነቃቃው ይሆን?

**አስቴር ኤልያስ**

መንግሥት ከሰሞኑ አጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራምን አስመልክቶ መግለጫ መስጠቱ ይታወቃል። ይህንኑ መግለጫ ተከትሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓቱን አሻሽሏል። ባንኩ፣ ከሐምሌ 22 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮም ሥራ ላይ ያዋለው ማሻሻያ ኢትዮጵያን ተወዳዳሪ ወደሆነውና በገበያ ላይ ወደተመሰረተው የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት እንደሚያሸጋግራት አመላክቷል። በኢኮኖሚ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተንሰራፍቶ የቆየውን የማክሮ ኢኮኖሚ አለመረጋጋትና መዛባት እንደሚሻሻልም ይታመንበታል ሲል አስረድቷል። የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያው በአዲሱ የውጭ ምንዛሪ መመሪያ መሰረት የሚተገበር እንደሚሆንም አብራርቷል።

ኢትዮጵያ፣ ገበያ መር የውጭ ምንዛሬ ተመን ሥርዓት ተግባራዊ ማድረጓን ተከትሎ ሰሞኑን ባንኮችም አዲሱ የምንዛሬ ተመንን መተግበር ጀምረዋል። ገበያ መር የውጭ ምንዛሬ ተመን ሥርዓቱ ተግባራዊ ከመሆኑ አስቀድሞ የአንድ ዶላር ዋጋ 58 ብር አካባቢ ቢሆንም፤ በአሁኑ ወቅት ሥርዓቱ ተግባራዊ በመሆኑ ይህ አኃዝ ወደ 100 ብርና ከዚያ በላይ ማሻቀቡ የሚታወቅ ነው። በጥቁር ገበያው ሲቸበቸብ ከነበረው ዋጋ ጋርም ያለው ልዩነት እየጠበበ መምጣቱም የአደባባይ ምስጢር ነው።

ይሁንና መንግሥት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ተግባራዊ ከማድረጉ ጋር ተያይዞ ገበያ መር የውጭ ምንዛሬ ተመን ሥርዓት ተግባራዊ በመሆኑ የብር የመግዛት አቅም ተዳክሟል። ይህን ተከትሎም ጥቂት የማይባሉ ነጋዴዎች ቀደም ሲል የነበራቸውን ሸቀጥ በመሰወራቸው የሸቀጥ ዋጋ መናሩ እየተነገረ ይገኛል፤ ነገር ግን መንግሥት ደግሞ ሸቀጥ በሚሰውሩና ዋጋ በሚጨምሩ ነጋዴዎች ላይ በግልጽ እርምጃ እየወሰደ መሆኑ ይታወቃል።

ከዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያይዞ የውጭ ምንዛሪ ተመን በገበያ ዋጋ እንዲካሄድ መወሰኑ ጠቀሜታው ምንድን ነው? አስፈላጊነቱስ ምን ይመስላል? የዋጋ ጭማሪ በሚያደርጉ ነጋዴዎች ላይ እርምጃ እየተወሰደ መዝለቅስ ይቻል ይሆን? ለሚሉ ጥያቄዎች በዘርፉ የዳበረ ልምድ ያላቸው አቶ ኤርሚያስ አመልጋ ከሸገር ኤፍ.ኤም 102 ነጥብ አንድ ሬዲዮ ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስና የማክሮ ኢኮኖሚ ባለሙያው ቴዎድሮስ መኮንን (ዶ/ር) ለሪፖርተር ጋዜጣ ያጋሩትን ሃሳብ ለጽሑፋችን በዋቢነት ተጠቅመናል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ኤርሚያስ አመልጋ፣ መንግሥት ሰሞኑን ይፋ ያደረገው ውሳኔ እንዲያውም የዘገየ ነው ባይ ናቸው። ለሁለት አስርት ዓመታት በዚህ ፖሊሲ ዙሪያ ሲናገሩ መቆየታቸውን ደጋግመው የገለጹት አቶ ኤርሚያስ፣ "የእኛ ሀገር ኢኮኖሚ እያንዳንዱ ሴሉ በካንሰር ተይዟል። ካንሰር ማለት ደግሞ ከአንድ እስከ አራት ድረስ የተለያዩ ደረጃዎች አሉት። ከአራተኛ ደረጃ ቀጥሎ ይገድላል። እኛም ልክ በኢኮኖሚያችን ያለፉት አስራ አምስትና ሃያ ዓመት ውስጥ ከደረጃ አንድ ካንሰር በሒደት ደረጃ አራት ካንሰር ውስጥ ገብተናል። ስለዚህም በጽኑ ታመናል፤ ለምን ቢባል በተሳሳተ ፖሊሲ ምክንያት ነው። አሁን ግን መድኃኒቱ ተገኝቷል " ይላሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ አሁን መታከም አለብን። ሕክምናው ደግሞ ያማል። የካንሰር ሕክምና ደግሞ መርዝ ነው። የካንሰር ሴሎችን የሚገድል ነው። ነገር ግን ደግሞ ለይቶ መግደል አይችልም። መድኃኒቱን ፈርተን አንወስድም ማለት ግን የሚያስከትለው ሞት ነው። ስለዚህ በረጅም ጊዜ የመጣ ችግር ዝም ብለን ምንም ሳይሰማን የምናልፈው ነገር አይደለም። ግን ደግሞ መሆን አለበት። ይሁንና በተለይ አቅም የሌለው ሕዝብ እንዳይጎዳ ድጎማ አስፈላጊ ነው። በቂ ነው ወይ ከተባለ ግን አይደለም። ለግሸበቱ መድኃኒት የሚሆነው ኢንቨስትመትና የገበያ ዓርዓት መስተካከል ሲችል ነው። አሁን የተወሰደው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ማስታገሻ ሳይሆን መሰረታዊ መድኃኒቱ ነው።

> **ጥቁር ገበያ የትም ሀገር ውስጥ አይቀርም። እንቅስቃሴ እስካለ ድረስ ይኖራል። ዋናው ነገር ጥቁር ገበያው መኖሩ ሳይሆን በጥቁር ገበያው ያለው እንቅስቃሴ ምን ያህል ተፈላጊነቱ ይቀንሳል የሚለው ነው። ይህ እንዲሆን ግን በባንክና በጥቁር ገበያው መካከል ያለው የምንዛሪ ዋጋ በጣም መቀራረብ አለባቸው**

የማክሮ ኢኮኖሚ ባለሙያው ቴዎድሮስ መኮንን (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ በአሁኑ ወቅት የፖሊሲው ተግባራዊ መሆን ትክክለኛ ጊዜው ነው ሲሉ ጠቅሰው፤ ከዚህ ሊያልፍ የሚያስችል ጊዜ ግን የለንም ይላሉ። ለተግባራዊነቱ ሌላ ቀጠሮ መያዝ እንደማይቻልም ይናገራሉ። ባለፈው ዓመት አንድ ዶላር በጥቁር ገበያ 95 ብር እየተመነዘረ ባለበት ሰዓት ገበያውን ነፃ እናድርገው ሲባል 'እስኪ ይቆይ!' ተብሎ ምንም ለውጥ ሳይደረግ አንድ ዶላር 120 ብር ገባ። አሁንም ገበያውን ሳናስተካክል 140 ብር ይገባል። ስለዚህ ቁጭ ብሎ በመጠበቅ የሚመጣ ለውጥ አይኖርም ሲሉ ይናገራሉ።

የማክሮ ኢኮኖሚ ባለሙያው ቴዎድሮስ (ዶ/ር) እንደ አቶ ኤርሚያስ ሁሉ ፖሊሲው ተግባራዊ ሲደረግ ሕመም እንዳለው ያመለክታሉ። የገንዘብ ምንዛሪን በገበያ ዋጋ ማድረግ ሊያስከትል የሚችለው ሕመም አንዱ መገለጫ ነጋዴው ሸቀጥ መደበቁና የዋጋ ንረቱ ሊሆን እንደሚችል ያስረዳሉ። በምርት መሸሸግ ምክንያት በተወሰነ ደረጃ ገበያውን ሊረብሹ የሚችሉ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። አንዱ መፍትሔ መንግሥት ያወጣውን ፖሊሲ ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ እስኪሆን መሥራት ነው ሲሉ ያብራራሉ። በዚህ ረገድ ምንም ማወላወል ሳያደርግ በፖሊሲው መሠረት በአግባቡ ሥራዎች መሠራታቸውን መከታተልና መቆጣጠር ተገቢ ነው ይላሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ የተወሰደው ርምጃ ጠቃሚና አስፈላጊ ነው። የውጭ ምንዛሪ ገበያው የተበላሸ ስለነበር መስተካከል ነበረበት። አሁን የተወሰደው ርምጃ ይህን ብልሽት የነበረበትን የውጭ ምንዛሪ ገበያችንን የሚያስተካክል ነው። ነገር ግን ችግሩ ሥር የሰደደ ስለነበር ለችግሩ መፍትሔ ይሆናል የተባለው ርምጃ ሲወሰድና ሲስተካከል ሕመም አለው። ይሁንና ሕመምን ይዞ መቀመጥ አይቻልም። ሕመሙን በማለፍ ማስተካከል የግድ ነው ሲሉ የአቶ ኤርሚያስን ሃሳብ ያጸናሉ።

ለምሳሌ አንድ ሰው ከባድ ሕመም ላይ ሆኖ ቀዶ ሕክምና ቢያስፈልገው ቀዶ ሕክምናው የሚያመጣበትን ሕመም ፈርቶ ህክምና ሳያደርግ አይቀርም። አሁን የተወሰደውን ርምጃ የማየው እንደዚያ ነው። ቀዶ ሕክምናው ሕመምተኛውን ለጊዜው ከአልጋ እንዳይነሳ ያደርገዋል። ዋናው ነገር ከሕክምናው በኋላ መንቀሳቀስ መቻሉን ማስጠበቅ ነው። ገበያው የሚሠራበትን መንገድ ከፍቷል። ገበያው ጤናማ ሆኖ እንዲሠራ ማስቀጠል ይጠበቅበታል። የተወሰደው ዕርምጃ ከዚህ አኳያ እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ የመሆኑን ያህል ብቸኛው ጉዳይ ተደርጎ ግን መወሰድ የለበትም።

መንግሥት ያወጣውን አዋጅ ላነበበ ሰው አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት... ተብለው በደንብ የተቀመጡ ነገሮች አሉ የሚሉት ደግሞ አቶ ኤርሚያስ ናቸው። አሁን ባንኮች ዘንድ ሲስተም ውስጥ የሌሉ ዶላሮች ከአሁን በኋላ መግባት እየጀመሩ ነው። ይህ ማለት አሁን አዋጁ ላይ ቁጭ ያለ ነገር አለ ማለት ነው፤ ቀደም ሲል መንግሥት ከባንኮች ከሚያገኘው የውጭ ምንዛሬ 50 በመቶ ይወስድ ነበር። አሁን ግን 'አልወስደውም፤ ይቀመጥ፤' አለ፤ ይህ ስንት ዶላር ነው ቢባል በግርድፍ ሦስት ቢሊዮን ዶላር ነው። መንግሥት ከሁሉም ባንኮች በብሔራዊ ባንክ በገባ ቁጥር 50 በመቶ የሚወስደው ማለት ነው። መንግሥት ይህንን 'ትቼላችኋለሁ' አለ። ከመቼ ጀምሮ ከተባለ ጉዳዩ ይፋ ከሆነበት ዕለት ጀምሮ ማለት ነው ሲሉ ያብራራሉ።

ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ነጋዴዎቹም እምብዛም ስላልገባቸው ይጨምራል በሚል ግምት ዶላሩን ይዘዋል። በተመሳሳይ ባንኮቹም ካለማወቅ የተነሳ ይዘውታል። ነገር ግን በቀጣዮቹ 12 ወራት ውስጥ ባንኮች ጋ ገብቶ ብሔራዊ ባንክ ይወስደው የነበረውን ሦስት ቢሊዮን ዶላር አሁን ባንኮች ጋ ይቀራል። ይህ በፖሊሲ ለውጥ ብቻ የመጣ ነገር ነው። ፖሊሲ የመጨረሻ ከባድ መሳሪያ ነው። ምክንያቱም በአንድ ፊርማ በፊት ወደ መንግሥት ይሔድ የነበረ ሦስት ቢሊዮን ዶላር አሁን ባንኮች ጋ ሊቀር ነው። ያ ማለት ደግሞ አሁን ሦስት ቢሊዮን ዶላር ከጥቁር ገበያ ወጣ ማለት ነው። ይህ አንዱ ጉዳይ ነው ይላሉ።

አቶ ኤርሚያስ እንደሚናገሩት፤ ሌላው ቢቀር ይህ ፖሊሲ ባንክ ሔደን የዶላር አካውንት እንድንከፍት ይፈቀድልናል። ስለዚህ ከውጭ ሀገር ዶላር ቢላክልን በዶላር ይቀመጥልኝ፤ አይመንዘር ማለት ይቻላል። ይህ በራሱ ወደጥቁር ገበያ ሊገባ የሚችልን ከውጭ የተላከ ገንዘብ (Remittance) ወደባንክ ሊያመጣ ይችላል። ወደ ባንክ ሲስተሙ ገባ ማለት ለሚፈልግ ሰው ተደራሽ የሚሆን ነው ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው ለሕክምና ውጭ ሀገር መሄድ ፈልጎ መቶ ሺ ዶላር አስፈልጎት ባንክ ጠየቀ እንበል፤ ጥያቄው ተቀባይነት አግኝቶ ውሰድ ይባላል፤ በስንት ይላል አሁን ለጊዜው 74 ነው ይባላል። ሌላውም እንዲያ ቢል ብሩ እስካለ ድረስ መልሱ ትችላለህ ነው።

አሁን የሚሰጥ ከተገኘ ማንም ሰው የውጭ ብድር መውሰድ ይችላል። አሁን ደንበኛው ሔዶ ባንኮችን ዶላር ስጡኝ ልመና ይቀርና ባንኮች መጥተው እባካችሁ ከእኔ ግዙ ማለታቸው አይቀሬ ነው።

አቶ ኤርሚያስ፤ አሁን ዶላር መግባት እየጀመረ ነው፤ በቀጣዮቹ ስድስት ወራት ውስጥ ደግሞ በደንብ መጉረፍ ይጀምራል። ያኔ ዶላሩን ይዞ መቀመጥ አስቸጋሪ ነው። ዶላር የሚፈልግን አካል ማሳደድ የግድ ይሆናል ይላሉ። እንዲያውም እርሳቸው እንደሚሉት፤ ማስታወቂያ ሁሉ ሊጀመር ይችላል ነው። "አሁን በእኛ አውድ የውድድር ሜዳው ተከፍቷል» ሲሉ የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ ያመለክታሉ።

ጥቁር ገበያ በአንድ ምሽት ሊጠፋ አይችልም የሚሉት ደግሞ የማክሮ ኢኮኖሚ ባለሙያው ቴዎድሮስ (ዶ/ር) ሲሆኑ፣ በባንኮችና በጥቁር ገበያው መካከል ያለው ልዩነት እየጠበበ ከመጣ፣ ቀስ በቀስ የጥቁር ገበያ እንቅስቃሴ በጣም ይቀንሳል ይላሉ።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ጥቁር ገበያው ስላለ በገበያ ዋጋ መገበያየት አልሠራም ማለት አይደለም። ጥቁር ገበያ የትም ሀገር ውስጥ አይቀርም። እንቅስቃሴ እስካለ ድረስ ይኖራል። ዋናው ነገር ጥቁር ገበያው መኖሩ ሳይሆን በጥቁር ገበያው ያለው እንቅስቃሴ ምን ያህል ተፈላጊነቱ ይቀንሳል የሚለው ነው። ይህ እንዲሆን ግን በባንክና በጥቁር ገበያው መካከል ያለው የምንዛሪ ዋጋ በጣም መቀራረብ አለባቸው። የዋጋ ተመኑ ካልተቀራረበ ኤክስፖርተሮችና ከውጭ ገንዘብ የሚልኩ ሰዎች በቀጣይም ጥቁር ገበያውን እየተጠቀሙ ይቀጥላሉ ማለት ነው። ወደ ትክክለኛው የምንዛሪ ቦታ የሚመጡት ተመኑ ሲቀራረብ ብቻ ነው። የባንክ የምንዛሪው ተመን ወደ ጥቁር ገበያው ዋጋ መጠጋት አለበት። ባንኮች በራሳቸው ተመን ማውጣት ስለተፈቀደላቸው እነሱም የዶላር እጥረት ስላለባቸው ዶላር ወደነሱ የሚያመጡትን ለማበረታታት ገበያው ወደሚከፍለው ጠጋ ማለታቸው አይቀርም ሲሉ ያብራራሉ።

ዋናው በበጎ የሚታይበት ጉዳይ ግን ገበያውን ያስተካክላል ተብሎ ስለሚታመን ነው የሚሉት የማክሮ ኢኮኖሚ ባለሙያው፤ በተለይ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ ወይም በወጪ ንግድ ላይ ለተሰማሩ ነጋዴዎች ትክክለኛ ዋጋቸውን እንዲያገኙ ያስችላል ሲሉ ይጠቅሳሉ። በአንድ ዶላር 58 ብር ሲያገኙ የነበሩ ምንዛሪው ዋጋ 100 ብር የሚገባ ከሆነ የቡና፣ ሰሊጥ ላኪዎች የተሻለ ዋጋ ያገኛሉ። ይህ አንዱ በጎ ጎኑ መሆኑን አመልክተው፤ ሌሎች ጠቀሜታዎችም እንዳሉት ይገልጻሉ። ገበያው ለሁሉም እኩል በሆነ የመሮጫ ሜዳ ውስጥ እንዲሆን ያደርጋል ሲሉም የአቶ ኤርሚያስን ሃሳብ ያጠናክራሉ።

ከዚህ በፊት የውጭ ምንዛሪ በቀላሉ ሲያገኙ የነበሩት መንግሥትና ጥቂት ባለሀብቶች ብቻ ናቸው ሲሉም አስታውሰው፤ አሁን ግን ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ሁሉም ሰው ያገኛል እንደ ማለት ነው ብለዋል። አሉታዊ ተብሎ የሚጠቀሰው ደግሞ ኢምፖርት የሚደረጉ ዕቃዎች ዋጋ የሚወደድ በመሆኑ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ እየተረጋጋ የነበረውን የዋጋ ንረት መልሶ እንዲወጣ ያደርጋል የሚል ሥጋት አለ ሲሉ ስጋታቸውን ይጠቁማሉ። ይህ ደግሞ በተለይ ዝቅተኛ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚጎዳ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ኤርሚያስ አባባል፤ የመርካቶ ነጋዴ አፍኖ ያስቀመጠውን እቃ ቢበዛ ከአራት ወራት በኋላ ለምኖ የሚሸጥበት ጊዜ ይሆናል። አሁን ዳኛው ገበያው ነው፤ ፖሊሲው ደግሞ ተቆጣጣሪው ነው። ከገበያው ፍላጎት ጋር መሄድ ነው፡። በተቃራኒ ከሄድን እንጠፋለን፤ ስለዚህ ዶላር አሁን እጥረት አይኖርም፤ ይህ እውቀትና ግንዛቤ አልባ አካሔድ ከሁለትና አራት ወር ድረስ ሊፈነጭ ይችላል። በኋላ ግን የሚከስም ነው። ውድድር እየመጣ ነው። የምንዛሪ እጥረት እየጠፋ ነው።

ማሻሻያውን ተከትሎ የውጪዎችም እንደሚመጡ ጠቁመው፤ በቀጣዩ ዓመት የምናየው ሌላ ሜዳ ነው ሲሉ አመልክተዋል። እርሳቸው እንዳሉት፤ አሁን ያሉ ተጫዋቾች ይህን ተገንዝበው መነቃቃት አለባቸው። ንግድ ባንክን መከተል ትተው የራሳቸውን እቅድ አውጥተው መሯሯጥ አለባቸው። አሁን የመጣው ፖሊሲ ያመቻቸው ሜዳ ቢኖር ይህንን ነው። በአጠቃላይ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ አዕምሮና የደም ዝውውር ሊኖረው ነው ብለዋል።

ምሁራኑ እንደሚሉት፤ ማሻሻያውን ተከትለው የሚመጡ ሕመሞች የሚያሰቃዩት ለጥቂት ጊዜ ነው። ግፋ ቢል የተወሰደው መድኃኒት እስኪሰራ ድረስ ነው፤ መድኃኒቱን ባለመጠቀም በዚህ ሕመም ውስጥ ሆኖ መዝለቅ ግን ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ሞት ነውና ጊዜያዊ የሆነውን ሕመም በመታገስ ጤናማ የሆነ መስመር ላይ መሆን አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው። ስለዚህም የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የበለጠ ተነቃቅቶ እንዲጓዝ መንግሥት ያወጣውን ፖሊሲ ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ እስኪሆን መሥራት የግድ ነው።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ችግር ያልበገራት እንስት

አመለወርቅ ከበደ

የሚያጋጥሙን የሕይወት ፈተናዎች መማሪያ ወይም ለመውደቂያችን ምክንያት ይሆናሉ። ከችግር ተምሮ የራስን ቀጣይ ኑሮ የተሻለ ለማድረግ መጣር ስኬት የመሆኑን ያህል፤ ካለፈው ትምህርት በመውሰድ ሌሎች በዚህ መንገድ እንዳያልፉ ትምህርት መስጠት እና አርአያ መሆን የስኬቶች ሁሉ ቁንጮ ነው።

አንዳንዴ ለችግር መጋለጣችን ሌሎች ምክንያት እንደሚሆኑት ሁሉ፤ ለሰው መድኃኒቱ ሰው ነው እንዲሉ፤ ከችግር ለመውጣታችን፣ ለስኬት የመብቃታችን የአንበሳውን ድርሻ የሚወስዱ ሰዎችም አይጠፉም።

እነዚህን በተቸገርንበት ጊዜ እጃቸውን የዘረጉልንን ቅኖች ለመርዳት የግድ እነሱ እስኪቸገሩ መጠበቅ ላይኖርብን ይችላል። ሌሎች እኛ ካሳለፍናቸው ሁኔታዎች ጋር እየታገሉ ያሉ ብዙ ነፍሶች አሉና እነዚህን ተመልሶ መርዳት የሚያስመሰግን ተግባር ነው።

በዚህ ደግሞ አንዱ የምንረዳበት መንገድ ያሳለፍነውን ወጣ ውረድ ለሌሎች ብርታት እንዲሆን በመንገር ነው። ይህን መርህ በተግባር ማሳየት ከቻሉ ሴቶች መሀል ደግሞ የዛሬዋ ባለታሪካችን አንዷ ናት።

የዛሬዋ ባለታሪካችን የተለያዩ የሕይወት ፈተናዎች ርሃብን፣ ጥሙን እና የሚደርስባትን ጥቃት ተቋቁማ ማለፍ የቻለች እናት ናት። እነዚህ ችግሮች ሳይበግሯት ሁለት ልጆችን ከጎዳና አንስታ አሳድጋለች። ያጋጠሟትን ችግሮች በምትጋፈጥበት ወቅት የአካባቢው እና የወረዳው ድጋፍ አልተለያትም ነበር። የተደረገላትን ውለታ ሳትረሳ አሁን ለበርካቶች ድጋፍ በማድረግ እየረዳች ትገኛለች።

በሰራችው በጎ ሥራዎች የተለያዩ ዋንጫዎች፤ ሜዳሊያዎች፣ የምስክር ወረቀት ተሸልማለች። በተጨማሪም ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሽልማት ተበርክቶላታል። ይህቺ በጎ አድራጊ ጌጤነሽ ኃይሌ ትባላለች። በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ በበጎ ፈቃድ ሥራ እና ማስተባበር ለ11 ዓመታት እያገለገለች የምትገኝ ሴት ናት። ትውልዷ በኦሮሚያ ክልል አምቦ ከተማ ሲሆን፤ ትምህርቷን እስከ ስምንተኛ ክፍል ነበር የተማረችው።

«ትምህርቴን የተከታተልኩት በአዲስ አበባ ከተማ ኮከበ ፅባህ ትምህርት ቤት ነው። የተማርኩት እስከ ስምንተኛ ክፍል ነው» ስትል ትገልጻለች። አንዳንዴ ያልጠበቅነው እና ያላሰብነው ነገር ወደ ሕይወታችን ይመጣና የሕይወት አቅጣጫችንን እንድንቀይር ያስገድደናል። ባለታሪካችን ከነበረችበት የሕይወት መንገድ አቅጣጫዋን ለመቀየር የሚያስገድድ ነገር አጋጠማት።

«ትምህርቴን ስምንተኛ ክፍል እየተማርኩ ሳለ እናቴ በድንገት ስትሞትብኝ ትምህርቴን መቀጠል አልቻልኩም። ምክንያቱም ሊያስተምረኝ የሚችል ዘመድ ስላልነበረኝ ለሥራ ወደ ሌላ ክልል ሄድኩ»ስትል ታስረዳለች።ለሥራ በሄደችበት በአጋጣሚ ከባለቤቷ ጋር ተዋውቀው ትዳር መስርተው አምስት ልጆችን ወልደዋል። «አሁን ሁሉም ልጆቼ ቦታ ቦታ ይዘውልኛል» ትላለች።

ጌጤነሽ ትዳር መስርታ አምስት ልጆችን ብትወልድም፤ ከባለቤቷ ጋር በገጠማት ተደጋጋሚ አለመግባባት ምክንያት አብረው ሊዘልቁ አልቻሉም።

ጌጤነሽ ሰውን ለመርዳት ድህነት ያልበገራት እናት ናት። አምጣ ከወለደቻቸው ልጆች ውጭ፤ ለሌሎች ልጆችም እናት ለመሆን በቅታለች። ባለታሪኳ ያሳደገችው አምስት ልጆች ብቻ ሳይሆን፤ ሌሎች ሁለት ልጆችን ከጎዳና አንስታ ለወግ ለማዕረግ አብቅታለች።

ሁለቱን ልጆች ከጎዳና አንስታ ልታሳድግበት የቻለችበትን አጋጣሚ ጌጤነሽ ስትናገር «ልጆቹ ጎዳና ላይ ብርድና ፀሀይ ሲፈራረቅባቸው በተደጋጋሚ እመለከት ነበር» ስትል ታስረዳለች።«በተለይ አንደኛው ልጅ ከደቡብ ክልል ነበር የመጣው በጣም ነበር የሚያሳዝነው። ወስጄ አሳድጌው እስከ ዘጠነኛ ክፍል አስተምሬው ነበር። ነገር ግን እኔ ሳላውቅ በመከላከያ ተመዝግቦ ሄዶ ሞተ።»ትላለች።



ጌጤነሽ ኃይሌ

ከጎዳና ወስዳ ካሳደገቻቸው ልጆች አንደኛውን በሞት ብትነጠቅም፤ በአንደኛው የተካሰች ትመስላለች። አንዱ ያሳደገችው ልጅ በህክምና ትምህርት ተመርቆ እየሰራ እንደሚገኝ ትናገራለች።«አሁንም ቢሆን እንደዚህ ጎዳና ላይ የወጡ ልጆችን ስመለከት ዝም ብዬ አላልፍም።ከየት ነው የመጣቹት? ከገጠር ያመጣችሁ ምንድን ነው?» በማለት እጠይቃለሁ ትላለች።

ጌጤነሽ ያሳደገቻቸውን ሁለት ልጆች ከጎዳና ወስዳ ለማሳደግ የነበራት ኢኮኖሚ ጠንካራ የሚባል አልነበረም። ራሷን ለማስተዳደር በአንድ ፋብሪካ ተቀጥራ የምትሰራ ሲሆን፤ ከጎዳና ያነሳቻቸውን ልጆች ለማሳደግ ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎችን ለመሥራት ትሞክራለች።

«ቀን ቀን በበጎ ፈቃድ ማስተባበር ሥራ ወረዳ እሰራለሁ፤ ከዛ በኋላ ማታ 12 ሰዓት ወደምሰራበት የፋብሪካ ድርጅት እሄዳለሁ። እዛ ስሰራ አድሬ ጠዋት ነው የምወጣው» ትላለች። «ያለኝ የገንዘብ አቅም ዝቅተኛ ቢሆንም፤ ሌሎችን ስረዳ የተመለከቱ የሰፈር ሰዎች፤ "እሷ እኮ ከራሷ አልፋ ሌሎችን የምትረዳ ናት" እያሉ ይደግፉኛል። በተጨማሪም ወረዳዬም ያግዘኛል »ስትል ትገልጻለች።

ጌጤነሽ በተሰማራችበት የበጎ ፈቃድ ሥራ በተለያዩ ዘርፎች ተሰማርታ ድጋፍ ትሰጣለች። የግንዛቤ ትምህርት በመስጠት ችግር ላይ ያሉ ሰዎች ራሳቸውን መለወጥ እንዲችሉም ታስተምራለች። ጌጤነሽ እንደምትናገረው ጎዳና ላይ ለወጡ ሴቶችና ሕፃናት ሕይወታቸውን መቀየር እንዲችሉ እና ሰርተው እንዲለወጡ ከራሷ ተሞክሮ በመነሳት ትምህርት ትሰጣለች። «ጥቃትም የደረሰባት ሴት ካለች እምባዋን አብሼላት እስከ ፍርድ ቤት ድረስ እወስዳታለሁ ስትል» ታስረዳለች።

ጥቃት ለደረሰባቸው በምን መልኩ ወደ ህግ እንደሚሄዱ የምታስረዳው ወ/ሮ ጌጤነሽ፤ ከህግ አወሳሰን ጋር በተያያዘ ለምሳሌ፤ አንዲት ሴት ላይ የመደፈር ጥቃት ተፈጽሞ ጥቃት አድራሹ ላይ ስድስት ዓመት ብቻ የሚፈረድበት ከሆነ ይግባኝ በማለት አብራ ከተጠቂዋ ጋር እንደምትቆም ታስረዳለች ።

ይህንንም ስራ ስትሰራ ከአዲስ አበባ ሴቶች ማህበር ጋር በጋራ እንደሚሰሩ ታስረዳለች። አስፈላጊ ሲሆንም ጠበቃ በነጻ ሊቆምላቸው እንደሚችል ትናገራለች። «አንዳንንድ ጊዜም ራሴ የምሄድባቸው ጉዳዮች ይኖራሉ። ፍርድ ቤት ላይ በሴቶች ጥቃት ላይ የሚሰሩ አካላት ስልካቸው አለኝ። የደረሰውን ጥቃት በዝርዝር እነግራቸው እና ወደ ማጣራት ስራ እንዲገቡ አደርጋለሁ» ትላለች።

**ጌጤነሽ ያሳደገቻቸውን ሁለት ልጆች ከጎዳና ወስዳ ለማሳደግ የነበራት ኢኮኖሚ ጠንካራ የሚባል አልነበረም። ራሷን ለማስተዳደር በአንድ ፋብሪካ ተቀጥራ የምትሰራ ሲሆን፤ ከጎዳና ያነሳቻቸውን ልጆች ለማሳደግ ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎችን ለመሥራት ትሞክራለች**

«ለምሳሌ ባለፈው አንድ አባት ልጁ ላይ የመድፈር ጥቃት ፈጸመ። ከዛን ከህግ አካላት ጋር በመሆን ወደ ቦታው ሄደን በማጣራት፤ ልጅቷን መጠለያ ስላለን ወደ መጠለያ አስገባናት፤ ሰውየው በፖሊስ እንዲያዝ ተደርጎ ክስ ተመሰረተባቸው» ስትል በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን በምን መልኩ እንደሚከላከሉ ታስረዳለች።

በሌላ በኩል ደግሞ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ሲያጋጥማት ቀስ ብላ በመጠጋት፤ ደላላው እየወሰዳቸው ካሉ ሰዎች ጋር በመቀላቀል እና አብራ የምትሄድ በመምሰል በማጣራት፤ ለህግ አካላት ችግሩን በመጠቆም መፍትሄ ለማግኘት ትሞክራለች።

ጌጤነሽ በምትሰራቻው ስራዎች ምንም አይነት የገንዘብ ክፍያ አይከፈላትም። የበጎ ፈቃድ ስራዎች እንዳይቋረጥ ምሽት ከሚሰሩት ስራ በተጨማሪ ወደ ሀብታም ቤት በመሄድ የተለያዩ ስራዎችን ትሰራለች።«ጠዋት ከስራዬ ወጥቼ ወደ ወረዳ እስከምመጣ ድረስ ሁለት መኪናዎችን አጥባለሁ። ከዛ በኋላ ወረዳ መጥቼ የሚሰራ ስራ ካለ ቶሎ እጨርስና ወደ ቀታና እሄዳለሁ» ትላለች።

«ልጆች ይገፔ በርካታ የርሃብ እና የችግር ግዚያትን አሳልፌያለሁ» የምትለው ጌጤነሽ፤ የምትሰራቻው ስራዎች ከችግር እንዳላቀቋት ትናገራለች። ስራዎቹ በሴት ያልተለመዱ ቢሆንም፤ ስለለመድኳቸው አይከብደኝም በማለት ትናገራለች።

ጌጤነሽ ሌሎች ሴቶችን በመጨመር ድግስ ባለባቸው ቤቶችም ሄዳ ትሰራለች። ስራ አጥተው እቤት ቁጭ ካሉ ሴቶች አንድ ወይ ሁለት ሴቶችን ከእኔ ጋር በመያዝ ሄጄ በመስራት ሁላችንም ተጠቃሚ እንድንሆን አደርጋለሁ ስትል ታስረዳለች።

ወደ በጎ ፈቃድ ስራ ከአስር ዓመት በላይ እንደሆናት የምትናገረው ጌጤነሽ፤ በሰራቻቸው የበጎ ፈቃድ ስራዎች በከተማ ደረጃ በተከታታይ አንደኛ በመውጣት ትታወቃለች። በአጠቃላይም ሶስት ዋንጫ እና ሜዳሊያዎችን ተሸልማለች። «በአንድ ወቅት ባለቤቴ ጥቃት እያደረሰብኝ ስለተቸገርኩ፤ዋንጫዎቹን እያነሳ እየወረወረብኝ ብዙ ፈተና ስላየሁኝ፤ ወንድሜ ጋር እንዲቀመጡ አደረኩ» የምትለው ጌጤነሽ፤ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ተንቀሳቃሽ ስልክ መሸለሟን ትናገራለች።

ጌጤነሽ በኑሮዋ ደካማ መሆኗን በመረዳት አሁን የምትኖርበትን ቤት ወረዳው ነው ሰርቶ የሰጣት። እሷም በተራዋ አቅም የሌላቸውን ሰዎች በመለየት ቤት እንዲሰራላቸው በመጠቆም የተከፈላትን ውለታ መልሳ ለመክፈል እየጣረች ነው።

«ሰዎችን ለመርዳት ጊዜ አልወስድም። ጉዳይ ቢኖርብኝ እንኳን ከበጎ አድራጎት በላይ የማስቀድመው ነገር አይኖረኝም» የምትለው ጌጤነሽ፤ የበጎ ስራ በምትሰራበት ወቅት ሰዎች እየደወሉ እንዳያስቸግሯት ስልኳን ጭምር እንደምታጠፋ ትናገራለች።

የበጎ ፈቃድ ስራው ከጌጤነሽ አልፎ ልጇቿ ጋር ጭምር እንደገባ ትናገራለች። ለበጎ ፍቃድ ስራ ልጇቿ ጭምር ስሱ ልብ እንዳላቸው ታስረዳለች። «ትልቋ ልጄ ጤና ጣቢያ ነው የምትሰራው፤ ከስራ አድራ ስትመጣ ያለውን ስራ ትሰራለች፤ እሷ ስትሄድ ደግሞ ሌሎች ልጆቼ ወደ ቤት ስለሚመለሱ የቤት ውስጥ ስራውን እየተጋገዙ ይሰራሉ፤በዚህም ህይወትን እየተጋገዝን እንመራታለን »ትላለች።

የጌጤነሽ የልጅነት ህልም የተቸገሩትን ሰብስቦ መርዳት ነበር። ለሰዎች ጥሩ ማሰብ፣ የተቸገሩን ማንሳት ነበር ።ይኸው ምኞት አሁን እውን መሆኑ እንዳስደሰታት ትናገራለች። «ለሰው ልጅ ቅድሚያ እሰጣለሁ፤ ተቸግረው ወደ ወረዳ እያለቀሱ ሲመጡ አብሬ አልቅሼ፣ የተራቡትንና የተጠሙትን ባለኝ አቅም አብልቼ አጠጥቼ ሌላ ችግር ካለባቸውም በተቻለኝ አቅም ደግፌ ከጎናቸው እቆማለሁ» የምትለው ጌጤነሽ፤ ይህን ስታደርግ የውስጥ እርካታ እንደሚሰማት ትናገራለች።

ጌጤነሽ እንደምትለው በጎ ስራ እርካታ ይሰጣል። ያለንን ነገር ለሌሎች ማካፈል ትልቅ ደስታ ያጎናጽፋል።« ድሮ እኔ ልብስ አልነበረኝም የዚህ የወረዳው አመራሮች ናቸው ያለበሱኝ » ስል ያለፈችበትን ችግር ታስታውሳለች።«ዛሬ እኔ ባለ ልብስ መሆን ችያለሁ። ስለዚህ እንደኔ ለተቸገረች ሴት ካለኝ አንድ ቀሚስ ብሰጣት ለእኔ እረፍት ነው። ሌሎችን ሳስተምር፤ ድሮ እኔ እንዲሁ ነበርኩ ነው የምለው። ስለዚህ ያጣም ያገኛል፤ ያገኘም ያጣል » ስል ታስረዳለች።

ባለታሪኳ እንደምትናገረው፤ ወደ ወረዳ ተቸግረው እያለቀሱ የሚመጡ ሴቶች ሲኖሩ፤« ወደ ጌጤነሽ ሂዱ»ይባላሉ። እሷ ጋር ሂዱና ተሞክሮ ውሰዱ በማለት ወደ እሷ ይላካሉ። «እኔ ጋር ሲመጡ አጽናናቸዋለሁ፤ ከዚህ በፊት እኔም በርካታ ችግሮችን እንዳለፍኩ አስረዳቸዋለሁ። እናም በችግር ውስጥ ላሉት የማስተላልፈው በትግስት ሁሉም ያልፋል በርቱ የሚል ነው» ስትል ትናገራለች።

የጌጤነሽን ምክር በመስማት አሁን ላይ ሰርተው ማደር እና ለሌሎችም ድጋፍ ማድረግ የጀመሩ መኖራቸውን ታስረዳለች። እናም በቀጣይ ባላት አቅም የተቸገሩትን ለመርዳት ትልቅ ፍላጎት እንዳላትና ከራሷም ተሞክሮ በመነሳት ሴቶች ወድቀው እንዳይቀሩ የበኩሏን እገዛ እንደምታደርግ በመናገር ሃሳቧን ቋጭታለች።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

በርካታ ዓመታትን ወደ ኋላ መለስ ብለን በኢትዮጵያ ምን አይነት ኩነቶች እንደነበሩ የምናስታውስበት አዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን ለዛሬ በርከት ያሉ ጉዳዮችን ያስቃኘናል። ለዚህም በተለይም በ1950ዎቹና 70ዎቹ የነበሩ ዘገባዎችን መርጠናል። ከመራረጥናቸው ዘገባዎች መካከል የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ 67ኛ ዓመት የልደት በዓል አከባበር፣ የሶቪየት ኅብረት ሕጻናት ስጦታ፣ 28 ሠራተኞች ሳንሠራ ደሞዝ ይከፈለናል ስለማለታቸው፣ 22 ጠንቋዮች እራሳቸውን ስለማጋለጣቸው፣ የ40 ዓመት ሴትም በአንድ ጊዜ 3 ልጆችን መገላገላቸው የሚያስታውሱን ዋነኞቹ ናቸው። በመጨረሻም "አብረን እንሳቅ አብረን እንኑር" እያልን፤ ከሚለው ገጽ ላይ ሁለቱን በመምረጥ አሰናድተን እንደሚከተለው አቅርበናል።

**የኢትዮጵያ ሕዝብ የተወዳጁን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የስድሳ ሰባተኛውን ዓመት የልደት በዓል እጅግ ከፍ ባለ ደስታ ያከብራል**

ይህ ዘመን የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አርቆ አስተዋይነት በአሜሪካና በኤውሮፓ፣ በእስያ፣ በአፍሪካ ክፍለ ዓለማት ከሚገኙት የወዳጅ አገሮች ጋር የኢትዮጵያን ሕዝብ በፍቅርና በወዳጅነት ያስተሳሰሩበት አዲሱ ሰለሞን የተባለው የግርማዊነታቸው ሰውነት በመላው ዓለም ውስጥ ዓለምን ያስደነቁበት ጊዜ ነው።

ከዚህም በቀር ደግሞ ይህ የዛሬውን የልደት በዓል ብዙ ዘመን ሙሉ በአስደናቂ ሥራ ሲጌጥ ለቆየው ለግርማዊነታቸው ዘመነ መንግሥት ወደ 68 ዓመት መተላለፊያ በር ስለሆነ ከፍ ባለ ሁኔታ እናከብረዋለን።

**ሐምሌ 16 ቀን 1954 ዓ.ም የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘ ኢትዮጵያ የስድሳ ሰባተኛው የልደት በዓል አከባበር ፕሮግራም**

1ኛ. ሐምሌ 16 ቀን 1954 ዓ.ም ከጠዋቱ 12 ሰዓት 21 መድፍ ይተኮሳል

2ኛ. ግርማዊት እቴጌ መነን በታላቁ ቤተ መንግሥት ውስጥ በኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ፀሎት ያደርሳሉ

3ኛ. ግርማዊት እቴጌ መነን ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ተኩል መሳፍንት፣ መኳንንቶች፣ ወይዛዝርቶችና የመንግሥት ሠራተኞች፣ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የሆኑት ነጋዴዎችና ታላላቅ ሰዎች በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ይቀበላሉ

4ኛ. በአራት ሰዓት ተኩል ግርማዊት እቴጌ መነን በቤተ መንግሥት ሠገነት ወጥተው ለተሰበሰበው ሕዝብ ይታያሉ። በዚህ ጊዜ በከተማው በአዲስ አበባ ሕዝብና በራሳቸው ስም ንግግር ያደርጋሉ።

5ኛ. በስድስት ሰዓት የውጭ አገር መንግሥታት እንደራሴዎች በቤተ መንግሥቱ የክብር መዝገብ ላይ ስማቸውን ይፈርማሉ።

**ልብስ ሚሊቴር ወይም ገበርዲን**
**ሲቢል ሞርኒንግ ኮት**
**ወይዛዝርቶች የከተማ ልብስ**

6ኛ. ግርማዊት እቴጌ መነን በስድስት ሰዓት ስለ በዓሉ ክብር መንግሥት ለኢትዮጵያ መሳፍንት ሚኒስትሮች፣ መኳንንቶችና ለመንግሥት ሠራተኞችና ለካህናቶች፣ በከተማው ነዋሪ ለሆኑት ታላላቅ ግብዣ ያደርጋሉ።

7ኛ. በዚሁ ቀን ከምሽቱ በ2 ሰዓት ስለ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በዓል ክብር የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቲያትር ቤት የራት ግብዣ ያደርጋሉ።

ልብስ ነጭ ክራባት

ከዚህ በኋላ የበዓሉ ፍጻሜ ይሆናል።

**(አዲስ ዘመን ሐምሌ 16 ቀን 1954ዓ.ም)**

**የሶቪየት ኅብረት ሕጻናት ለኛ ሕጻናት ስጦታ ላኩ**

በሶቪየት ሕብረት በኪርጌዚያ ሪፐብሊክ የተለያዩ መንደሮች የሚኖሩ ሕጻናት በትርፍ ጊዜያቸው በእርሻ ቦታዎች በመሥማራት እየሠሩ ባጠራቀሙት ገንዘብ የገዟቸውን አሻንጉሊቶችና ልዩ ልዩ መጫዎቻዎች ለኢትዮጵያ ሕጻናት እንዲውል በርዳታ ልከዋል።

........

ስጦታውን የላኩት የሶቪየት ኅብረት ሕጻናት የኢትዮጵያ ሕጻናት የደስታ ኑሮ እንዲኖሩ እንደሚታገሉ ከስጦታው ጋር በላኩት ደብዳቤ ማረጋገጣቸውን ጓድ አምባሳደር ኪርናሶቪ ስኪይ ገልጠዋል።

**(አዲስ ዘመን የካቲት 24 ቀን 1971 ዓ.ም)**

**28 የገጠር ፕሬዜዎች ሠራተኞች ሳንሠራ ደመወዝ ይከፈለናል ይላሉ**

በገጠር ፕሬዜዎች ድርጅት በአዋሳ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት 28 አናጢዎችና ግንበኞች ለአራት ወራት ሥራ በማስፈታት 14ሺህ 892 ብር ደመወዝ በነፃ የከፈላቸው መሆኑንና በመሥሪያ ቤቱ ውስጥም ከፍተኛ የሥራ መዝረክረክ መኖሩን ከገጠር ፕሬዜዎች ድርጅት አጠቃላይ የሠራተኞች ማኅበር ጽሕፈት ቤት ሁኔታውን እንዲያጣራ የተላከው ቡድን አጋለጠ።

**(አዲስ ዘመን ሚያዚያ 12 ቀን 1971ዓ.ም)**

**የ40 ዓመት ሴት በአንድ ጊዜ ሦስት ልጆች ወለዱ**

ሐረር (ኢ.ዜ.አ) ወይዘሮ ፋጡማ ኢብሮ የተባሉት የ40 ዓመት ሴት ሐረር ከተማ በሚገኘው በምሥራቅ አርበኞች ሆስፒታል ውስጥ ባለፈው ዓርብ 3 ሕጻናትን በአንድ ጊዜ መገላገላቸውን አቶ ሽፈራው አቢቢ የሆስፒታሉ አስተዳደር አስታወቁ።

ከሕጻናቱም መካከል መጀመሪያ የተወለደው ወንድ 4 ኪሎ ከሃያ አምስት ግራም ክብደት ሲኖረው ተከትለው የተወለዱት ሌሎች አንድ ወንድና ሴት ደግሞ እያንዳንዳቸው አንድ ኪሎ ከ20 ግራም ክብደት እንዳላቸው ተገልጧል።

**(አዲስ ዘመን ግንቦት 7 ቀን 1971ዓ.ም)**

**22 ጠንቋዮች ራሳቸውን አጋለጡ**

**ደሴ,(ኢ.ዜ.አ)** ወሎ ውስጥ በደላንታ ወረዳ የኢላና ትምህርት ቤት መምህራን ከጣርዳት፣ ከደህናንና ከዝባን የገበሬ ማኅበራት ጋር በመተባበር በመካከላቸው የተሰገሰጉትን 22 ዓባይ ጠንቋዮች ራሳቸውን አጋልጠው ክቡር ወደሆነው የሥራ መስክ እንዲሠማሩ አደረጉ።

እነዚሁ 22 ዓባይ ጠንቋዮች በተሰጣቸው ትምህርት አምነው ድቤዎችን(ከበሮዎችን)፣ እንዲሁም በእጃቸው ይገኙ የነበሩትን ልዩ ልዩ የጥንቆላ ዕቃዎችንና መጽሐፍት ለገበሬ መኅበራቱ በራሳቸው ፈቃድ አስረክበዋል። ዓባይ ጠንቋዮቹ ካስረከቧቸው ዕቃዎች ውስጥ በተለይ ከበሮዎቹ በአካባቢው ለሚቋቋመው የኪነት ቡድን መገልገያ እንዲሆን መሰጠቱ ተገልጧል።

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 23 1971 ዓ.ም)**

**አብሮ መሣቅ**
**አብሮ መኖር**
**ከቤቱ ሠርግ አለው**
**ስትተኛ ሙቃ**
**ስትኖር ተሳስቃ**
**ስትሄድ ገንዘብ ንቃ።**

ሺጋ መልከ መልካም ድቡልቃ ሚስት ያለው ከሰው ሠርግ አይሄድም ከቤቱ ሠርግ አለው።

**ስትኖር ተነዛንዛ**
**ስትተኛ ቀዝቅዛ**
**ስትሄድ ገንዘብ ይዛ።**

ነዝናዛ የሆነች ፈዛዛ ሚስት ያለው ከሰው ለቅሶ አይሄድም ከቤቱ ለቅሶ ነው።

.........

ቃጫ ፋብሪካ

ሸበቶ:- የኔ ወንድም ይህ አስፋልት ወዴት ይወስዳል?

መላጣ:- ቃጫ ፋብሪካ ያደርስኃል

**(አዲስ ዘመን መስከረም 20 ቀን 1958 ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ ባሕር ሰርጓጅ ሚሳኤል ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ላከች

በጋዜጣው ሪፖርተር

አሜሪካ ውጥረት ወደተባባሰበት መካከለኛው ምሥራቅ ባሕር ሰርጓጅ ሚሳኤል ላከች። ከባሕር ሰርጓጅ ሚሳኤሉ ቀድሞ የሚደርስ የአየር መሣሪያ እንደተላከም የአሜሪካ መከላከያ ፀሐፊ ሎይድ ኦስተን ገልጸዋል።

ከፍተኛው የሐማስ መሪና ከፍተኛ የሄዝቦላህ አመራሮች መገደላቸውን ተከትሎ ቀጣናዊ ግጭት እንደሚፈጠር ተሰግቷል። አሜሪካም ስጋቱን ተከትላ መሣሪያዎቿን ልካለች። አሜሪካ መሣሪያዎቹን መላኳ እሥራኤልን ከኢራን ለመከላከል ቁርጠኛ መሆኗን ያሳያል ሲሉ ሎይድ ኦስተን ተናግረዋል። "አጋራችንን ለመከላከል ማንኛውንም አማራጭ እንከተላለን" ብለዋል።


ኢራን ለሐማስ ከፍተኛ የፖለቲካ መሪ ኢስማኤል ሐኒያ ግድያ መቼ እና እንዴት አፀፋዊ ምላሽ እንደምትሰጥ እየተጠበቀ ይገኛል። በሐኒያ ግድያ ኢራን እሥራኤልን ተጠያቂ አድርጋለች። እሥራኤል ከግድያው ጀርባ እንዳለች በስፋት ቢታመንም ስለ ጉዳዩ ምንም አላለችም።

ዩኤስኤስ ጆርጅያ የተባለውን ባሕር ሰርጓጅ ሚሳኤል አሜሪካ መላኳን ፔንታጎን ባወጣው መግለጫ ጠቁሟል። ኤፍ-32 ሲ ተዋጊ ጀት የያዘው ዩኤስኤስ አብርሃም ሊንከን ወደ መካከለኛው ምሥራቅ እንዲበርም ትዕዛዝ ተሰጥቷል። ኢራን ምን እያቀደች እንዳለ ግልጽ አይደለም።

እሥራኤል ላይ ጥቃት ሊሰነዝር የሚችለው ሄዝቦላህም ጭምር ነው። የሄዝቦላህ ከፍተኛ ኮማንደር ፉዓድ ሹክር መገደሉን ተከትሎ ሄዝቦላህ አፀፋዊ ምላሽ እንደሚሰጥ አስታውቋል።

በካታር፣ ጆርጅታውን ዩኒቨርሲቲ የሚያስተምሩት ፕሮፌሰር መርሀን ካማራቫ እንዳሉት፣ አሜሪካ በይፋ ባሕር ሰርጓጅ መላኳ "ኢራን እና ሄዝቦላህን ለማስፈራራት" ያለመ ነው። "ኢራን አንዳች ነገር እያቀደች ነው። ጥቃት መሰንዘሯ አይቀርም" ብለዋል።

ወደ መካከለኛው ምሥራቅ በርካታ በረራዎች ተሰርዘዋል። ሉፍታንዛ ወደ ቴል አቪቭ፣ ቤሩት፣ ኤርቢል፣ ቴህራን እና ኦማን እስከ አውሮፓውያኑ ነሐሴ 21 ድረስ በረራ መሰረዙን አስታውቋል። ኤር ፍራንስም ወደ ቤሩት በረራ የሰረዘ ሲሆን፣ ስዊዝ ኤር ወደ ቴል አቪቭ እና ቤሩት በረራ አቋርጧል። ኤርባልቲክ እና ኢዚጀት አየር መንገዶችም በረራ እንደሚሰርዙ ገልጸዋል።



ከወራት በፊት ሶርያ ውስጥ ያለው የኢራን ቆንስላ ላይ ጥቃት መሰንዘሩን ተከትሎ ኢራን እሥራኤል ላይ ጥቃት መሰንዘሯ ይታወሳል። በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰው አልባ አውሮፕላኖች እና ሚሳኤሎች ወደ እሥራኤል ተተኩሰዋል።

የጆ ባይደን አስተዳደር በጋዛ የተኩስ አቁም ተደርጎ እስራኤላውያን ታጋቾች እንዲለቀቁ ለማድረግ ንግግሩን እንደሚቀጥል አስታውቋል። ሐማስ በበኩሉ እስራኤል ለድርድር የቀረቡትን ነጥቦች መቀበል እንዳለባት ለአሜሪካ ገልጿል። ሆኖም በንግግር ለመሳተፍ ፈቃደኛ መሆኑን ቡድኑ አክሏል።

አሜሪካ ከዚህ ቀደም የተደረጉ ንግግሮች ያልተሳኩት በሐማስ ምክንያት ነው ብትልም፣ የእሥራኤል መገናኛ ብዙኃን እንደሚሉት አሜሪካ ቀኝ ዘመም ጥምር ፓርቲ ያላቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁን ስምምነት ባለማድረግ ተጠያቂ ታደርጋለች።

ዋይት ሃውስ ባለፈው ሳምንት በይፋ እሥራኤላዊውን የገንዘብ ሚኒስትር ቤዛሊል ስሚትሮች ወቅሷል። ሚኒስትሩ እሥራኤል አሜሪካ ያቀረበችውን የተኩስ አቁም ስምምነት እንዳትቀበል ይገፋፉሉ። የዋይት ሃውስ ብሔራዊ ደኅንነት ቃል አቀባይ ጆን ኪርቢ ሚኒስትሩ "ስህተት ሠርተዋል" ብለዋል።

ዩናይትድ ኪንግደም፣ ፈረንሳይ እና ጀርመን የተኩስ አቁም እንዲደረግ ይሻሉ። "ከዚህ በኋላ መዘግየት እንደሌለበት እንስማማለን። መረጋጋት እንዲሰፍን እና ነገሮች እንዳይባባሱ ጥረት እንቀጥላለን" ሲሉ መግለጫ አውጥተዋል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## እስራኤል በአየር ኃይል ወታደሮቿ ላይ የጉዞ እገዳ ጣለች

በጋዜጣው ሪፖርተር

እሥራኤል በአየር ኃይል ወታደሮቿ ላይ የጉዞ እገዳ ጣለች፡፡ ከ10 ወራት በፊት ሐማስ በእስራኤል ምድር ድንገተኛ ጥቃት መሰንዘሩን ተከትሎ ነበር በመካከለኛው ምሥራቅ ጦርነት የተቀሰቀሰው፡፡ አንድ ሺህ 200 ሰዎች በሐማስ ጥቃት ተገድለውብኛል ያለችው እስራኤል ከሁለት ሳምንት በፊት የድርጅቱ የፖለቲካ እና ወታደራዊ መሪዎችን ገድላለች።

በጋዛ የተጀመረው ይህ ጦርነት በየጊዜው መልኩን እየቀያየረ ወደ ሊባኖስ እና የመን እየተስፋፋ ሲሆን በቀጣይ ደግሞ በሌሎች አካባቢዎችን ሊሰፋ እንደሚችል ስጋት አይሏል፡፡

በተለይም በኢራን ተመራጩ ፕሬዚዳንት በዓለ ሲመት ላይ ለመገኘት ወደ ቴህራን ያመሩት የሐማሱ የፖለቲካ መሪ እስማኤል ሀኒየህ መገደል ተጨማሪ ውጥረት ፈጥሯል፡፡

ግድያው በግዛቷ የተፈጸመባት ኢራን እሥራኤልን ተጠያቂ ያደረገች ሲሆን እሥራኤል መቀጣት እንዳለባት እና ርምጃ እንደምትወስድ ዝታለች፡፡

እሥራኤል ከኢራን፣ ሂዝቦላህ እና በሌሎች ሀገራት የሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች አማካኝነት ጥቃት ይደርስብኛል በሚል በተጠንቀቅ ላይ መሆኗን አስታውቃለች፡፡



ግብፅ እና ጆርዳንን ጨምሮ ሌሎችም ሀገራት ወደ እሥራኤል የሚተኮሱ የአየር ላይ ጥቃቶችን እንደሚያከሽፉ አስቀድመው አስጠንቅቀዋል፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ እሥራኤል የአየር ኃይል ወታደሮቿ ወደ ውጪ ሀገራት እንዳይጓዙ ያስጠነቀቀች ሲሆን ወታደሮቹ በኢራን እና አጋሮቿ ዒላማ ሊዳረጉ እንደሚችሉ በመስጋት ነው፡፡

አሜሪካ በበኩሏ እስራኤልን ከጥቃት ለመጠበቅ ተጨማሪ የጦር መሣሪያዎችን አስቀድማ ወደ ስፍራው የላከች ሲሆን ተጨማሪ ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች እንዲላኩም መወሰኑን ሮይተርስ ዘግቧል፡፡

የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ባሳለፍነው ሳምንት ኢራን እና አጋሮቿ በእሥራኤል ላይ የተቀናጀ ጥቃታቸውን በሦብት ቀናት ውስጥ እንደሚያደርሱ አስጠንቅቆ ነበር፡፡

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾቻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት:- www.press.et
ፌስቡክ:- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን ማክሰኞ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የኦሊምፒክ ቡድኑ ዛሬ እውቅናና ሽልማት ተዘጋጅቶለታል

**ብርሃን ፈይሳ**

በ33ኛው የፓሪስ ኦሊምፒክ የተሳተፈው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ዛሬ ማለዳ ወደ ሃገሩ ተመልሷል። ከ800 ሜትር እስከ ማራቶን ባሉት የአትሌቲክስ ውድድሮች የተካፈለው ልዑካን ቡድን 1 የወርቅ እና 3 የብር በጥቅሉ 4 ሜዳሊያዎችን ማስመዝገቡ ይታወቃል። ከዓለም 47ኛ ከአፍሪካ ደግሞ 4ኛ ደረጃን የያዘው ቡድኑ ጠዋት 12 ሰዓት ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር መንገድ ሲደርስም በከፍተኛ የመንግሥት ሥራ ኃላፊዎች አቀባበል ተደርጎለታል።

ኢትዮጵያ ከሜልቦርን እስከ ፓሪስ በተካሄዱ 15 የኦሊምፒክ መድረኮች ላይ ተወካዮቿን ያሳተፈች ሲሆን፤ በዚህም 24 የወርቅ፣ 13 የብር እና 23 የነሐስ በጥቅሉ 62 ሜዳሊያዎችን ማስመዝገብ ችላለች። ከትናንት በስቲያ በተጠናቀቀው የፓሪስ ኦሊምፒክ ተሳትፎዋ እንደተጠበቀው ባይሆንም በተለያዩ ርቀቶች ሜዳሊያዎች ተገኝተዋል። የወርቅ ሜዳሊያው በጀግናው አትሌት ታምራት ቶላ የማራቶን ውድድር ሲመዘገብ የኦሊምፒክ ክብረወሰንን በመስበርም አትሌቱ የድርብ ድል ባለቤት ሊሆን ችሏል። በሴቶች ማራቶንም እጅግ ጠንካራ በነበረው ፉክክር የዓለም ክብረወሰን ባለቤቷ ትዕግስት አሰፋ የብር ሜዳሊያ አጥልቃለች። በ10ሺ ሜትርም አትሌት በሪሁ አረጋዊ እና ወጣቷ የ800 ሜትር አትሌት ፅጌ ድጉማ የተቀሩትን የብር ሜዳሊያዎች አስገኝተዋል።




በፓሪስ ኦሊምፒክ የተሳተፈው ልዑካን ቡድን ዛሬ በብሔራዊ ቤተመንግሥት ዕውቅናና ሽልማት ተዘጋጅቶለታል፣

በወንዶች 3ሺ ሜትር መሰናክል የዓለም ክብረወሰን ባለቤቱ አትሌት ለሜቻ ግርማ ተጨማሪ የወርቅ ሜዳሊያ የሚያገኝበት ሰፊ ዕድል ቢኖረውም ውድድሩን ሊያጠናቅቅ ሲቃረብ በመውደቁ በአሳዛኝ ሁኔታ ፉክክሩን ማጠናቀቅ አልቻለም። በሌላ በኩል በአጨራረስ እንዲሁም ውድድርን ከማንበብና ተወዳዳሪን የተለየ ስልት ከመከተል ጋር የተገናኘ ስህተት በተለያዩ ርቀቶች ሜዳሊያዎች እንዳይመዘገቡ ምክንያት ሆኗል። ኢትዮጵያ ቀድሞም የታወቀችበትና ‹‹አረንጓዴው ጎርፍ›› የሚል ቅጽል ያገኘችበት እንዲሁም ለውጤታማነቷ ከፍተኛ ሚና ሲጫወት የቆየው የቡድን ሥራ በዚህ ኦሊምፒክ ጎልቶ አልታየም። በአትሌቶች ሊተገበሩ የተሞከሩ የቡድን ሥራዎችም በአግባቡ ተግባራዊ አለመሆናቸውም ታይቷል።

ወደ ፓሪስ ከነበረው ጉዞ አስቀድሞ ሲከሰቱ የነበሩ አነጋጋሪ ጉዳዮችና አወዛጋቢ አካሄዶች ውድድሩ በሚካሄድበት ስፍራም ተጠናክሮ የቀጠለበት ነበር። የስፖርት ቤተሰቡን አንገት ካስደፉ ድርጊቶች ባለፈ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ውድድሮች ሜዳሊያዎች ይመዘገቡባቸው በነበሩ ርቀቶች ተፎካካሪ ሆኖ አለመገኘትም ኢትዮጵያ በዝቅተኛ የሜዳሊያ ቁጥር ተሳትፎዋ እንዲደመደም አድርጓል። ከሲድኒ እስከ ሪዮ ባሉት 5 ኦሊምፒኮች ኢትዮጵያ ያስቆጠረቻቸው ሜዳሊያዎች በእያንዳንዳቸው 7 እና 8 ሲሆን፤ በቶኪዮ እና በፓሪስ ኦሊምፒኮች የተመዘገበው የሜዳሊያ ቁጥር ግን በእኩል 4 ብቻ ነው። የወርቅ ሜዳሊያ ቁጥሩም ወደ አንድ ከወረደ ከ2016ቱ ሪዮ አንስቶ ይህ ሦስተኛው ኦሊምፒክ ነው።

ኢትዮጵያ እአአ በ1980 የሞስኮ ኦሊምፒክ በሻምበል ምሩፅ ይፍጠር ‹‹ማርሽ ቀያሪው›› 5ሺ እና 10ሺ ሜትር ርቀቶች ሁለት የወርቅ ሜዳሊያ ከተመዘገበበት ጊዜ አንስቶ በተካሄዱት ኦሊምፒኮች በርቀቶቹ ስኬታማ ሃገር ልትሆን ችላለች። በዓለም አቀፍ ደረጃም የኢትዮጵያ መታወቂያ በሆኑት በእነዚህ ርቀቶች የቤጂንግ ኦሊምፒክ (እአአ 2008) በአትሌት ቀነኒሳ በቀለ እና ጥሩነሽ ዲባባ በሁለቱም ርቀት አሸናፊነት 4 የወርቅ ሜዳሊያዎች የተገኙበት በታሪክ ስኬታማው ውድድር ነው። በተቀሩት የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ተሳትፎዎችም ከእነዚህ ርቀቶች ቢያንስ በአንዱ አንድ የወርቅ ሜዳሊያ ይገኝ ነበር። በአንጻሩ ፓሪስ ላይ በወንዶች ምድብ አንድ የብር ሜዳሊያ ብቻ ከማስመዝገብ ባለፈ ኢትዮጵያ የቀደመ የርቀቱ የበላይነቷና ተፈሪነቷ አለመኖሩ የታየበት ሆኗል።

ማለዳ ላይ ወደሃገሩ የገባው የኦሊምፒክ ቡድን ዛሬ ከሰዓት በኋላ በብሔራዊ ቤተመንግስት የአቀባበል መርሐ ግብር ተዘጋጅቶለታል። በኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳሕለወርቅ ዘውዴ አማካኝነትም ውጤት ያስመዘገቡ አትሌቶች የክብር ሽልማት፣ የማበረታቻ እና የእራት ግብዣ መርሐ ግብር እንደሚኖር የኢፌዴሪ ባሕልና ስፖርት ሚኒስትር አስታውቋል።